የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ – ህዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 8
ADDIS ABABA - 20th Nov, 1998

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፬/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፰፻፷፮

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 44/1998
Federal prosecutor Administration Council of Ministers Regulations ........................ Page 866

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፬/፲፱፻፺፩
### ስለፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የወጣ
### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በዐቃብያነ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፸፬/፲፱፻፹፭ በአንቀጽ ፯ በተደነገገው መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፬/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፣

፩· "ዐቃቤ ሕግ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት ደረጃዎች በአንዱ የተመደበ የፌዴራል መንግሥት ዐቃቤ ሕግ ነው ፤

፪· "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትሕ ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው ፤

፫· "ምክትል ሚኒስትር" ወይም "ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትሕ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ነው ፤

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO 44/1998
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF FEDERAL PROSECUTORS

These Regulations are issued by the Council of Ministers in accordance with Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.4/1995 and Article 7 of Attorneys' Proclamation No. 74/1993.

### PART ONE
### *General*

1. *Short Tittle*

   These Regulations may be cited as the "Federal prosecutor Administration Council of Ministers Regulations No. 44/1997"

2. *Definition*

   In these Regulations unless the context requires otherwise;

   1) "Prosecutor" means a Federal prosecutor appointed to any of the Grades as indicated in Article 5 of these Regulations;
   2) "Minister" or "Ministry" means the Minister or the Ministry of Justice of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, respectively;
   3) "Vice Minister" or "Deputy Attorney General" means the vice Minister or Deputy Attorney General of the Ministry;

ያንዱ ዋጋ 6·00
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፬· "መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው ፤

፭· "ዋና ጉባዔ" እና "ንዑስ ጉባዔ" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፹፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተቋቋመ ጉባዔ ነው ፤

፮· "ተጠሪ ጽሕፈት ቤት" ማለት ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ የተቋቋመ የሚኒስቴሩ ተጠሪ ጽሕፈት ቤት ነው ፤

፯· "ደረጃ ወይም የሥራ ደረጃ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ሥር በተዘረዘረው መሠረት ዐቃብያነ ሕግ የተቀጠሩበት ፣ የተመደቡበት ወይም የተሾሙበት ደረጃ ነው ፤

፰· "ሹመት" ማለት አንድ ዐቃቤ ሕግ ከነበረበት ደረጃ ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚያድግበት ነው ፤

፱· "ደመወዝ" ማለት በዐቃቢያነ ሕግ የደመወዝ ስኬል መሠረት ለአንድ የሥራ ደረጃ የተወሰነ መነሻ ደመወዝና በየደረጃው ውስጥ በየጊዜው የሚሰጥ የደመወዝ ጭማሪ ነው ።

፫· የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ ፤

፩) ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ፤
፪) ምክትል ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ፤
፫) ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ ፤
፬) ዐቃቤ ሕግ ደረጃ አንድ ፤
፭) ዐቃቤ ሕግ ደረጃ ሁለት ፤
፮) ዐቃቤ ሕግ ደረጃ ሦስት ፤
፯) ዕጩ ዐቃቤ ሕግ ፤

ሆኖ በተመደበ ዐቃቤ ሕግ ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል ።

## ክፍል ሁለት
## ስለ ዐቃብያነ ሕግ አመራረጥ ፣ ቅጥርና ሹመት

፬· ለዐቃቤ ሕግነት የሚያበቁ ሁኔታዎች

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሆኖ የሚሾም ፤
ሀ) በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ፣
ለ) ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ታማኝ የሆነ ፤
ሐ) ከታወቀ ዩኒቨርስቲ በሕግ ትምህርት በዲግሪ ወይም በዲፕሎማ የተመረቀ ፤
መ) በታታሪነቱ ፣ በታማኝነቱ ፣ በፍትሐዊነቱና በሥነ-ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ ፤ እና
ሠ) ዕድሜው ፲፰ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ፤

፪· በዚህ ደንብ ስለ ዕጩ ዐቃቤ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በማንኛውም ደረጃ የሚቀጠር ወይም የሚሾም ዐቃቤ ሕግ ለደረጃው የተወሰነውን የመመዘኛ መስፈርት ማለትም ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ እንዲሁም እንደ ሁኔታው ልዩ ሥልጠና ማሟላት አለበት ።

፭· ስለዐቃቤ ሕግ ቅጥር አፈጻጸም ደንብ

፩· ሚኒስቴሩ ዐቃብያነ ሕግ ስለሚመደቡባቸው ክፍት የሥራ ቦታዎች ተስማሚ በሆነው መንገድ በሰፊው ማስታወቅ አለበት ። በሚያወጣውም ማስታወቂያ ወይም መግለጫ ውስጥ የተባለው ክፍት የሥራ ቦታ አጭር መግለጫ ፣ ተፈላጊ ችሎታዎች ፣ የሥራ ደረጃ ፣ የሚከፈለው ደመወዝና ሌላም አስፈላጊ መረጃዎችን ይይዛል ።

፪· በሚኒስቴሩ ውስጥ በዐቃቤ ሕግነት ለመቀጠር የሚወዳደሩ ሰዎች ሁሉ የቅጥር ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ማቅረብ አለባቸው ።

4) "Government" means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

5) "Higher commission" and "Lower commission" means comissions established pursuant to Article 88 of these Regulations, respectively;

6) "Branch office" means the office of the Ministry established in National Regional States;

7) "Grade or work grade" means grade of prosecutor employment, assignment or appointment as prescribed under Article 5 of these Regulations;

8) "Appointment" means the assignment of a prosecutor from one grade to a higher grade;

9) "Salary" means a starting salary and periodic increment given for a specific work grade in accordance with the salary scale of the Federal Prosecutors.

3. *Scope of Application*

These Regulations shall be applicable to the following prosecutors:

1) Assistant Attorney General;
2) Deputy Assistant Attorney General;
3) Higher Prosecutors;
4) Prosecutor Grade One;
5) Prosecutor Grade Two;
6) Prosecutor Grade Three;
7) Candidate Prosecutor.

## PART TWO
## *Selection, Employment and Appointment of Prosecutors*

4. *Qualification for Appointment of a prosecutor*

1) Any person to be appointed as a Prosecutor shall:
   (a) be an Ethiopian citizen
   (b) be loyal to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
   (c) be a graduate in law with a degree or diploma from a recognized university;
   (d) have distinguished himself by his diligence; loyalty, and good moral character; and
   (e) be 18 years of age or above.

2) Without prejudice to the provisions regarding candidate prosecutors, any prosecutor to be employed or appointed at any grade shall fulfill the requirement for the grade, namely, educational qualification and work experience and, as appropriate, special training.

5. *Procedure for employment of Prosecutors*

1) The Ministry shall notify in detail and in appropriate manner vacancies available for the assignment of prosecutor. The notice of vacancy shall contain a short description of the vacancies available for the assigment of prosecutor. The notice of vacancy shall contain a short description of the vacancy, required qualification, work grade, salary and any other appropriate information.

2) Candidates applying to be employed as prosecutors in the Ministry shall fill employment application form.

፫· ሚኒስቴሩ በቀረበለት የቅጥር ማመልከቻ መሠረት ለመቀጠር ተስማሚ መስለው የተገኙትን አመልካቾች በመፈተን ለሥራው ብቁ የሆነና ከተወዳዳሪዎች መካከል የተሻለውን አጠቃላይ ውጤት ያገኘውን ሰው ይመርጣል ።

፬· የፈተናው ይዘት በሚኒስቴሩ ያለውን የሥራ ዕድገትና ዐቃቤ ሕግ የሚቀጠርበትን ክፍት የሥራ መደብ ልዩ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ተፈታኙ ለሚወዳደርበት ደረጃ የሚበቃ ጠቅላላ ችሎታና ዕውቀት እንዲሁም ተሰጥኦ ያለው መሆኑን የሚመዝን መሆን አለበት ። ፈተናውም እንደአስፈላጊነቱ የቃል ወይም የጽሑፍ ጥያቄ በማድረግ ወይም ሁለቱን የፈተና ዓይነቶች በማጣመር ወይም በሌሎች የችሎታ መመዘኛዎችና ስልቶች በማጣራት ሊሆን ይችላል ።

## ፮· ማስረጃ ስለማቅረብ

በሚኒስቴሩ ውስጥ አዲስ የሚቀጠር ዐቃቤ ሕግ ከመቀጠሩ በፊት የሚከተሉትን አሟልቶ ማቅረብ አለበት ፤

፩· የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ፤

፪· የጤንነት ምርመራ ውጤት ፤

፫· ከወንጀል ነፃ ለመሆኑ የፖሊስ ማስረጃ ፤

፬· ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎች ።

## ፯· ስለጤንነት ምርመራ

፩· በመሥሪያ ቤቱ በዐቃቤ ሕግነት ለመቀጠር ተወዳድሮ በዕጩነት የተመረጠ አመልካች ለመቀጠር ይችል ዘንድ በቅድሚያ የጤና ምርመራ አድርጎ ማለፍ አለበት ።

፪· በዐቃቤ ሕግነት ለመቀጠር ተወዳድሮ በዕጩነት የተመረጠ አመልካች በጤና ረገድ ለሥራው ተስማሚ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚያቀርብበትን የምርመራ ዓይነት መ/ቤቱ ይወስናል ። በዚህም መሠረት ምርመራ እያደረጉ በመ/ቤቱ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የምስክር ወረቀት እንዲሰጡ እውቅና የተሰጣቸው ሐኪሞች ወይም የሕክምና ተቋሞችን መ/ቤቱ መወሰን ይችላል።

## ፰· ስለሹመት አሠጣጥ መሠረታዊ ደንቦች

፩· በአንቀጽ ፬ የተጠቀሰው ጠቅላላ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ደረጃ ፤ የሥራ ልምድ ፤ የሥራ አፈጻጸም፣ መልካም ሥነ ምግባር እና ለአዲሱ ኃላፊነት ያለው በጎ ፈቃድ ለሹመት አሠጣጥ መሠረት ናቸው ።

፪· ሹመት የሚሰጠው ለሥራው አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው ።

## ፱· ስለዐቃብያነ ሕግ አመራረጥና አሿሿም

፩· ለረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግነትና ለምክትል ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግነት የታጩት ሰዎች በምክትል ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሚኒስትሩ ይሾማሉ ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር ከተመለከቱት የሹመት ደረጃዎች በታች በሆነ ደረጃ ላይ የሚሾሙ ዐቃብያነ ሕግ በዋናው ጉባኤ አቅራቢነት በሚኒስትሩ ይሾማሉ ።

## ፲· ስለዐቃብያነ ሕግ ተጠሪነት

፩· ዐቃብያነ ሕግ ተጠሪነታቸው ለሚኒስትሩ ይሆናል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ ከእርሱ ለሚቀጥለው የበላይ ዐቃቤ ሕግ ተጠሪ ይሆናል ።

3) The Mimistry, based on the application forms, shall examine the candidates who seem fit and shall select the one with the best results.

4) The content of the examination shall take into account the work progress of the Ministry and the special nature of the vacancy concerned to evaluate the general knowledge and capability as well as the gift of the candidate. Where appropriate the examination may be oral or written or both or other method of evaluation may be used.

## 6. *Supporting Documents*

A new employee in the Ministry shall submit the following complete documents:

1) educational qualification and work experience documents;
2) health certificate;
3) Police certificate for not involving in criminal activities;
4/ other necessary documents.

## 7. *Medical Examination*

1) A candidate who is selected to be employed in the Ministry as an attorney shall pass medical examination.
2) The Minstry shall determine the requirements of medical fitness having regard to the nature of the work, and may designate medical practitioners or institution to make such examinations.

## 8. *Basic Principles for Appointment*

1) Subject to the general rules provided under Article 4, educational qualification, work experience, outstanding performance, good character and interest for the new position are basic principles for appointment.
2) An appointment shall be made only where it is necessary for the job.

## 9. *Selection and Appointment of Attorneys*

1) Assistant Attorney Generals and Deputy Assistant Attorney Generals shall be appointed by the Minster upon recommendation of the Vice Minister.
2) Prosecutors below the rank indicated under sub Article (1) of this Article shall be appointed by the Minister upon recommendation by the higer commission.

## 10. *Accountability of Prosecutors*

1) Prosecutors shall be accountable to the Minister.
2) Without prejudice to the provision of Sub Article (1) of this Article, a prosecutor at any level shall also be accountable to his immediate superior.

፲፩· ቃለ መሐላ ስለመፈጸም

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሆኖ የሚሾም ሰው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት አግባብ ባለው ባለሥልጣን ፊት ቀርቦ የሚከተለውን ቃለ መሐላ መፈጸም አለበት ፤

"እኔ ...................................................... ለሀገሬ ታማኝ በመሆን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትንና ሌሎች ሕጎችን ላከብርና ላስከብር ፤ በፌዴራሉ መንግሥት የወጡና ወደፊት የሚወጡ ሕጎችን በማስፈጸም የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ልሠራ ፤ የሥራ ድርሻዬን ሕግ በሚደነግገው መሠረት በመፈጸም የሰዎችን ክብርና ሰብአዊ መብት ላከብርና ላስጠብቅ ፤ የግል ጥቅም ሳልፈልግ ማንንም በመውደድ በመጥላት ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት አድልዎ ሳላደርግ ፤ ማንኛውንም ዓይነት ተጽእኖ ሳልፈራ በሃቀኝነት ፤ በቅንነትና በትጋት ኃላፊነቴን ለመወጣት ቃል እገባለሁ ።"

፪· መሐላውን ያስፈጸመው ባለሥልጣን የተፈጸመውን መሐላ በዐቃቤ ሕጉ የግል ማኅደር ውስጥ ይመዘግባል ።

፲፪· ስለዐቃቤ ሕግ ቅጥርና ሹመት መሠረዝ

አንድ ዐቃቤ ሕግ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የሐሰት ማስረጃዎችን አቅርቦ ቢቀጠር ወይም ቢሾም ይህ ሁኔታ ለዐቃቤ ሕግነት በተመረጠበት ጊዜ ታውቆ ቢሆን ኖሮ ቅጥሩን ወይም ሹመቱን አያስከለክለውም ነበር የሚያሰኝ ካልሆነ በቀር ቅጥሩ ወይም ሹመቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሠረዝ ይቻላል ።

፲፫· ስለሙከራ ጊዜ

፩· ከዩኒቨርስቲ በሕግ ትምህርት በድግሪ የተመረቀ ወይም በዲፕሎማ የተመረቀና አራት ዓመት ልምድ ያለው አዲስ ተቀጣሪ የሙከራ ጊዜው አንድ ዓመት ይሆናል ።

፪· በሌላ መሥሪያ ቤት በሕግ ሙያ አገልግሎ በዐቃቤ ሕግነት ለመቀጠር የተመረጠ ሰው የሚቀጠረው ለ፮ ወራት የሙከራ ጊዜ ይሆናል ።

፲፬· ቋሚ ሆኖ ስለመመደብ

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫ መሠረት በሙከራ የተቀጠረ ዐቃቤ ሕግ በተወሰነለት የሙከራ ጊዜ ለሥራው ተገቢ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የትምህርት ደረጃውና የሥራ ልምዱ በሚመጥነው ደረጃ ቋሚ ሆኖ ይመደባል ።

## ክፍል ሦስት
## የሥራ ሁኔታ
### ንዑስ ክፍል አንድ
### በሥራ ላይ ስለመገኘት

፲፭· ስለመደበኛ የሥራ ሰዓት

፩· የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሥራ ቀንና ሰዓት የዐቃቤያን ሕግ የሥራ ቀንና ሰዓትን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናል ።

፪· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ወደሥራው ዘግይቶ የመጣ እንደሆነ ወይም ቀደም ብሎ ከሥራው የወጣ እንደሆነ ወይም በአንድ ምክንያት ከሥራው የቀረ እንደሆነ ይህንኑ ለቅርብ ኃላፊው ማስታወቅ አለበት ።

፫· በመደበኛ የሥራ ሰዓት በሌላ ሥራ ወይም የሥራ ቦታ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ ይህንኑ ለቅርብ ኃላፊው መግለጽና ማስፈቀድ አለበት ።

፲፮· ከመደበኛው የሥራ ሰዓት በላይ ስለመሥራት

፩· ሥራው የሚመለከተው የበላይ ኃላፊ በአዘዘ ጊዜ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከመደበኛው የሥራ ሰዓት በላይ መሥራት ግዴታው ነው ።

11. *Oath*

1) Any peson who is to be appointed as a prosecutor shall, before assuming office, take the following oath beofore an appropriate authority:

"I ———————————————solemnly swear that I shall be loyal to my country and pledge to abide by the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and other laws, to work for the supremacy of law, to execute existing laws and those to be enacted in future by the Government, to carry out my responsibilities on the basis of the law, to respect human dignity and safeguard human right and that I shall discharge my duties honestly, sincerely, diligently and impartially without seeking personal gain and without fear or favor of any kind."

2) The authority who administered the declaration of oath shall record it in the personal file of the prosecutor.

12. *Nullity of Employment and Appointment*

An employment or appointment of any prosecutor, based on false inforamtion given by him intentionally or negligently, shall be declared null and void at any time, unless the information provided couldn't have been an impediment to the employment or appointment had it been known at the time of such of employment or appointment.

13. *Probation*

1) The probation period for a candidate prosecutor who graduated from university with a degree of Bachelor of laws or a diploma in law with four years relevant experience shall be one year.

2). The probation period for a person who has served in other institution as a lawyer and selected to be employed as a prosecutor shall be six months.

14. *Permanent Assignement*

Where a prosecutor on probation satisfactorily completes the period of probation as provided under Article 13 of these Regulations, he shall be assigned permanently in a positon he fits, having regard to his qualification and experience.

## *PART THREE*
## *Condition of Work*
### *Section one*
### *Attendance*

15. *Normal Hours of work*

1) The working days and hours of Government institutions shall be applicable to working days and hours of prosecutor.

2) Any prosecutor shall report his late arrival, early departure or other cases of absence to his superior.

3) A prosecutor engaged in a different work or place of work during normal hours of work shall declare same and obtain permission from his superior.

16. *Overtime*

1) Any prosecutor is obliged to work overtime when instructed by his superior.

፪· ዐቃቤ ሕጉ ከመደበኛው የሥራ ሰዓት በላይ እንዲሠራ የሚታዘዘው ሊያደርግለት የሚገባው ጥንቃቄና ድጋፍ ሁሉ ሳይጓደልበትና ሥራው በመደበኛ የሥራ ሰዓት ሊፈጸም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው ።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ስለ ፈቃድ

፲፯· የዓመት ዕረፍት ፈቃድ

፩· በማናቸውም የሥራ መደብ የተመደበ ዐቃቤ ሕግ ደመወዝ የሚከፈልበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል።

፪· ለዐቃብያነ ሕግ የሚሰጣቸው የዓመት ዕረፍት ፈቃድ እንደሚከተለው ይሆናል፡

ሀ) አንድ ዓመት ያገለገለ ዐቃቤ ሕግ ሀያ/፳/ የሥራ ቀናት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል ፡

ለ) ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገለ ዐቃቤ ሕግ ላገለገለበት ለያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ሀ" በተመለከተው የፈቃድ ጊዜ ላይ አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል። ሆኖም በዚህ አኳኋን የሚሰላው የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ከሰላሳ/፴/ የሥራ ቀናት መብለጥ የለበትም ።

፫· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው መሠረት የዐቃብያነ ሕግ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ሲሰላ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ በሌላ የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ የሠራበት ጊዜ በዐቃቤ ሕግነት ተመድቦ ከሠራበት ጊዜ ጋር ተደምሮ ይታሰባል። እንዲሁም ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት ልማት ድርጅት ተዛውሮ የመጣ ዐቃቤ ሕግ ወደሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ከመዛወሩ በፊት በሠራባቸው መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ውስጥ አገልግሎት ያበረከተበት ጊዜ ለዓመት ዕረፍት ፈቃዱ ስሌት ይታሰብለታል ።

፲፰· የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ

፩· የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ዘመን የሚባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጀት ዓመት ነው ።

፪· የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ሳይከፋፈል በአንድ ጊዜ በፈቃዱ ዘመን መወሰድ አለበት ። ሆኖም በአንዳንድ ልዩ ልዩ ምክንያት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ተከፋፍሎ ሊሰጥ ይችላል።

፫· የዓመት ፈቃድ የሚሰጠው በተቻለ መጠን የመሥሪያ ቤቱን ጥቅምና የዐቃቤ ሕጉን ፍላጎት በማመዛዘን በሚዘጋጀው ፕሮግራም መሠረት ነው ።

፲፱· የዓመት ዕረፍት ፈቃድን ስለማስተላለፍ

፩· አንድ ዐቃቤ ሕግ በሥራው አስፈላጊነት ምክንያት በፈቃዱ ዘመን የዓመት ዕረፍት ፈቃዱን ሙሉውን ወይም በከፊል ለመውሰድ ያልቻለ እንደሆነ ፈቃዱ ወደሚቀጥለው የፈቃድ ዘመን ይተላለፋል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የዓመት ዕረፍት ፈቃድን ማስተላለፍ የሚቻለው ቢበዛ ለሁለት (፪) ተከታታይ የፈቃድ ዘመን ብቻ ነው ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት ሳይሆን በሌላ ምክንያት በሙሉ ወይም በከፊል ያልተወሰደ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ቀሪ ይሆናል ።

2) Overtime work shall be ordered only if the work cannot be done during normal working hours and the prosecutor so instructed shall be given due care and the necessary support to the extent feasible.

## *Section Two*
## *Leave*

17. *Annual Leave*

1) A prosecutor shall have the right to annual leave with pay.

2) The following annual leave shall be granted to prosecutors.

(a) twenty (20) working days for a prosecutor who has served for one year;

(b) twenty (20) working days plus one wotking day for every additional year of service for a prosecutor who has served more than one year. However annual leave calculated in such a manner shall not exceed thirty (30) working days.

3) In calculating annual leave in accordnace with sub-Article (2) of this Article, the length of service rendered by a prosecutor in a different job within the Ministry or in other government institution or public enterprise before transferring to the Ministry shall be counted.

18. *Granting of Annual leave*

1) The annual leave year shall be the fiscal year of the Government.

2) Annual leave shall be taken without interruption at one time in the fiscal year. However, in special cases it my be permitted to take annual leave by installement.

3) Annual leave shall be granted in accordance with a schedule designed with due regard to the interest of the prosecutor and the Ministry.

19. *Postponing Annual Leave*

1) If the exigencies of the service unexpectedly prevent a prosecutor from taking his full annual leave or part of it within the leave year, it shall be postponed to the next fiscal year.

2) Any leave shall be postponed in accordance with sub Article 1 of this Article, only for a maximum of two consecutive leave years.

3) If for reasons other than those stated in sub Article (1) of this Article annual leave is not taken fully or partially it snall be forfeited.

፳· የሕመም ፈቃድ

፩· በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ የሙከራ ጊዜውን ከጨረሰ በኋላ በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ሳይሆን በሌላ ሕመም ምክንያት ሥራ ለመሥራት ካልቻለ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሕመም ፈቃድ ያገኛል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ፈቃድ ሕመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው የአሥራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በተከታታይ ወይም በተለያዩ ጊዜያት ቢወሰድም በማንኛውም ሁኔታ ከስድስት ወር አይበልጥም ።

፫· በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም አራት ዓመት ጊዜ ውስጥ የተሰጠው የሕመም ፈቃድ ድምር ስምንት ወር የደረሰ እንደሆነ ወደፊት ሌላ የሕመም ፈቃድ አይሰጠውም ።

፬· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በሕመም ምክንያት ከሥራ ሲቀር መሥሪያ ቤቱ ስለሁኔታው ሊያውቅ የሚችል ወይም ዐቃቤ ሕጉ ለማስታወቅ የማይችል ካልሆነ በቀር በማግስቱ ለመሥሪያ ቤቱ ያስታውቃል ።

፭· በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ በመታመሙ ምክንያት በተከታታይ ከሦስት ቀን በላይ ከሥራ ከቀረ መታመሙን የሚያረጋግጥ የሐኪም ምሥክር ወረቀት ማቅረብ አለበት ። የሐኪም ምሥክር ወረቀቱ ከዐቃቤ ሕጉ የግል ማኅደር ጋር ተያይዞ በምሥጢር መጠበቅ አለበት ።

፮· የሕመም ፈቃድ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ይሰጣል ፡

ሀ) ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ወራት ከሙሉ ደመወዝ ክፍያ ጋር ፤

ለ) ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ለእያንዳንዱ ወር ከግማሽ የወር ደመወዝ ክፍያ ጋር ፤

ሐ) ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ጊዜ ያለደመወዝ ክፍያ።

፳፩· የሕመም ፈቃድን ከዓመት የዕረፍት ፈቃድ ስለመቀነስ

፩· በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ የሐኪም ምሥክር ወረቀት ሳይኖረው በሕመም ከሥራ የቀረበት ቀን ተደምሮ ከስድስት /፮/ ቀን የበለጠ እንደሆነ ከስድስት /፮/ ቀን በላይ ያለው ጊዜ ከዓመት የዕረፍት ፈቃዱ ላይ ይቀነስበታል ።

፪· ዐቃቤ ሕጉ ከዓመት የዕረፍት ፈቃድ የተረፈ ቀን የሌለው ከሆነ ከስድስት ቀን በላይ ያለው ቀን በተከታዩ የፈቃድ ዘመን ከሚታሰብለት የዓመት ዕረፍት ፈቃዱ ላይ እንዲቀነስ ይደረጋል ። ይህ ካልተቻለም ያለደመወዝ እንደተወሰደ ፈቃድ ይቆጠራል ።

፳፪· የወሊድ እና የእርግዝና ፈቃድ

፩· ነፍሰጡር የሆነች ዐቃቤ ሕግ ከእርግዝናዋ ጋር የተያያዘ ምርመራ ለማድረግ መሥሪያ ቤቱ ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጣታል፡ ሆኖም ዐቃቤ ሕጓ ስለምርመራው ሐኪም ማስረጃ ማቅረብ አለባት።

፪· ነፍሰጡር የሆነች ዐቃቤ ሕግ ከመውለዷ በፊት ሐኪም እንድታርፍ ካዘዘ ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ታገኛለች ።

፫· ነፍሰጡር የሆነች ዐቃቤ ሕግ እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ቀን በፊት መውለጃዋ ሲደርስ የሰላሳ ተከታታይ ቀን የወሊድ ፈቃድ እንዲሁም ስትወልድ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ ፷ ተከታታይ ቀናት የወሊድ ፈቃድ ከደመወዝ ክፍያ ጋር ይሰጣታል።

*20. Sick Leave*

1) If a perosecutor at any level, having completed his probation, is rendered incapable of work owing to sickness other than those resulting from occupational injury, he shall be entitled to sick leave.

2) The leave referred to in sub-article(1) of this Article shall in no case be more than six months counted consecutively or separately in the course of any twelve months period starting from the first day of his sickness.

3) If a prosecutor at any level, has had eight (8) months sick leave in the aggregate in a period of four (4) years, no further sick leave shall be granted.

4) Where any prosecutor absents himself from work on grounds of sickness he shall notify the Ministry the day following his absence, unless the Ministry is in a position to know the sickness or unless it is impractical to notify.

5) When a prosecutor is absent form his work for more than three consecutive days due to sickness, he shall submit a medical certificate. The medical certificate shall be kept in his personal file confidentially.

6) Sick leave shall be granted in the following manner:

(a) for the first two months with full payment of his salary,

(b) for the next two months with 50% payment of his salary,

(c) for the next two months without pay.

21. *Deduction of sick leave from annual leave*

1) Where the aggregate number of days during which a prosecutor is absent from office, due to sickness without a medical certificate, exceeds six (6) days during the leave year the number of days exceeding six (6) shall be deducted from his annual leave.

2) In case no annual leave is left, the days shall be deducted from the next year's leave allowance, failing which the excess shall be considered as leave without pay.

22. *Maternity leave*

A pregnant prosecutor shall be granted:

1) Paid leave for medical examination in accordance with a doctor's recommandation.

2) Paid leave before delivery if recommended by a doctor.

3) A pregnant prosecutor shall be granted a period of 30 consecutive days of maternity leave with pay preceding the presumed date of her confinement and a period of 60 consecutive days of maternity leave after confinement.

፬· ዐቃቤ ሕግ ከመውለዷ በፊት የወሰደችው የሰላሳ ቀን ፈቃድ ሲያልቅ ካልወለደች እስከምትወልድበት ቀን ድረስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት እረፍት ልታገኝ ትችላለች ። የሰላሳ ቀን ፈቃዷ ሳያልቅ ከወለደች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የምትወስደው የወሊድ ፈቃድ ይጀምራል።

፳፫· የሐዘን ፈቃድ

፩· የማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሚስት ወይም ፣ ባል ፣ አባት ፣ እናት ፣ ወንድም ፣ እህት ወይም ልጅ ቢሞት ደመወዝ የሚከፈልበት የአምስት (፭) ቀን የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል።

፪· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ ከሞተበት በአንድ የፈቃድ ዘመን ውስጥ ከስድስት (፮) ቀን እስካልበለጠ ድረስ እስከ አንድ ቀን የሚደርስ ደመወዝ የሚከፈልበት የሐዘን ፈቃድ ይሰጠዋል ።

፳፬· ልዩ ፈቃድ

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ከደመወዝ ጋር ልዩ ፈቃድ የማግኘት መብት አለው ።

ሀ) ጋብቻውን በሚፈጽምበት ጊዜ የአምስት (፭) የሥራ ቀናት ፈቃድ ፣

ለ) ስለሚከታተለው ትምህርት ለሚወስደው ፈተና በማናቸውም ዓመት ፈተና ለሚወሰድባቸው ቀናት በሙሉ፣

ሐ) የጥናቱ ፕሮፖዛል በሚኒስትሩ ታይቶ ሲፈቀድ ለሕግ ጥናትና ምርምር ሥራ በ፭ ዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ ለሁለት (፪) ወር፣

መ) በማናቸውም ደረጃ ወደሚገኝ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ማናቸውም መርማሪ አካል እንዲቀርብ የሚያስገድደው መጥሪያ ሲያቀርብ የተፈለገ በትን ጉዳይ አከናውኖ ለመመለስ ለሚያስፈ ልገው ጊዜ፣

፪· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ፈቃድ የጠየቀበት ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ከሥራ ገበታ ተለይቶ በአገር ውስጥ ወይም ከአገር ውጭ በትምህርቱ ለማሳለፍ ሲሆን እና ትምህርቱን ተከታትሎ ሲያጠናቅቅ ለመሥሪያ ቤቱ የተሻለ አገልግሎት እንደሚያበረክት ሚኒስትሩ ሲያምንበት የትምህርት ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል ። ፍቃዱ የሚሰጥበት የጊዜ ርዝመት እና ሌሎች ሁኔታዎች መንግሥት በሚያወጣው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ይሆናል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚሰጠው የትምህርት ፈቃድ በየሁለት ዓመት ለሚደረግ የደመወዝ ጭማሪ ተፈላጊ ለሆነው የቆይታ ጊዜ አይታሰብለትም።

፳፭· ያለፈቃድ ከሥራ ስለመቅረት

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሳይፈቀድለት በማናቸውም ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ የቀረበት ጊዜ ደመወዝ እንዲያዝ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል።

፪· ዐቃቤ ሕግ ከሥራ ለቀረበት በቂ ምክንያት ያቀረበ እንደሆነ ከሥራ ለቀረበት ጊዜ ሙሉ ደመወዙን ወይም በከፊል ለማግኘት ይችላል።

፳፮· ስለፈቃድ አጠያየቅ

በጽሑፍ ለመጠየቅ የማይቻልበት ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የሚጠይቀው ፈቃድ ሁሉ በጽሑፍ መሆን አለበት።

4) If the pregnant proscutor does not deliver on the presumed date and the 30 days of her prenatal leave in accordance with sub-Article 2 of this Article has elapsed, the days subsequently taken before the beginning of the prenatal period shall be counted out of the regular annual leave within the fiscal year.

23. *Mourning Leave*

1) In cases of death of wife, husband, father, mother, brother, sister, son or daughter, a prosecutor shall be granted five (5) days mourning leave with pay.

2) If a close relative or a close friend dies, a prosecutor shall be granted upto one day mourning leave with pay, not exceeding, however, six (6) days during a leave year.

24. *Special Leave*

1) A Prosecutor has the right to be granted special leave with pay in the following conditions.

(a) for concluding marriage, five (5) working days;

(b) for all examination days during the year for the course he has been enrolled;

(c) to carry out legal research approved by the minister, two (2) months once in every five (5) years;

(d) when compelled to appear before any court or investigating authority, the necessary time for his appearance, on production of the summons.

2) Education leave may be granted to any prosecutor where the leave is required for pursuing studies locally or abroad, provided the minister is convinced that the prosecutor's training contributes to his rendering a service upon completion of his education. The duration and condition of the leave shall be based on the guidelines of the Government.

3) Education leave granted under sub article 2 of this Article shall not be considered for a two-year salary increment.

25. *Unauthorized absence*

1) Where a prosecutor is absent from duty without permission, the necessary arrangements for withholding his salary for the days of his absence shall be made.

2) If the prosecutor produces sufficient reasons for his absence, he may get full or partial payment for the time of absence.

26. *Application for leave*

All leave shall be requested in writing unless the prosecutor is encountred with situations preventing him to do so.

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለዝውውር

**፳፯. መሠረት**

አንድ ዐቃቤ ሕግ ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም ከአንድ የሥራ ዘርፍ ወደ ሌላ የሥራ ዘርፍ ተዛውሮ እንዲሠራ የሚደረገው ሚኒስቴሩ በሚያደርገው ድልድል መሠረት ወይም የሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ በሚያቀርበው የዝውውር ጥያቄ ይሆናል።

**፳፰. በሚኒስቴሩ ስለሚደረግ የዐቃብያነ ሕግ ዝውውር**

፩· ለሥራው አስፈላጊ ሲሆንና ሥራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመፈጸም ሲባል የሥራውን ግነስና መብዛት፣ የዐቃቤ ሕጉን ትጋትና የሥራ ውጤታማነት በማመዛዘን ማንኛውንም ዐቃቤ ሕግ የደረጃ መብትና ጥቅሙን ሳያጓድል ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም ከአንድ የሥራ ዘርፍ ወደ ሌላ የሥራ ዘርፍ ሚኒስቴሩ ሊያዛውር ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚኒስቴሩ በየጊዜው የሚፈጸም የዐቃብያነ ሕግ ዝውውር ጉባኤ ተጠንቶና በተቻለ መጠን በዕቅድ ተይዞ መከናወን ይኖርበታል።

**፳፱. በዐቃቤ ሕግ ስለሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ**

፩· በማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ በጽሁፍ ሆኖ በሚኒስቴሩ የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ አማካኝነት ለዋናው ጉባኤ መቅረብ አለበት።

፪· ዋናው ጉባኤ የቀረበውን የዝውውር ጥያቄ መርምሮ አስተያየቱን ለሚኒስትሩ ያቀርባል። ዋናው ጉባኤ አስተያየቱን ለሚኒስትሩ ከማቅረቡ በፊት ዝውውር የጠየቀውን ዐቃቤ ሕግ የበላይ ኃላፊ አስተያየት መጠየቅ ይችላል። ሚኒስትሩ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፫· በጤና ችግር ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት በሚኒስትሩ ካልተፈቀደ በቀር አንድ ዐቃቤ ሕግ የዝውውር ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት በተመደበበት ቦታ ቢያንስ ሁለት ዓመት ማገልገል አለበት ።

## ንዑስ ክፍል አራት
## ስለደመወዝ

**፴· የደመወዝ መደብ**

በልዩ ልዩ ደረጃ ለሚመደቡና ለሚሾሙ ዐቃብያነ ሕግ የሚከፈላቸው ደመወዝ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው በፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ የደመወዝ ስኬል መሠረት ይሆናል።

**፴፩· የመነሻ ደመወዝ**

አዲስ የሚመደብ ዐቃቤ ሕግ ለተመደበበት የሥራ ደረጃ የተወሰነው የመነሻ ደመወዝ ይከፈለዋል።

**፴፪· ሹመት ሲሰጥ ስለሚፈቀድ የመነሻ ደመወዝ**

፩· አንድ ዐቃቤ ሕግ ሹመት ሲሰጠው ከመሾሙ በፊት ሲያገኝ የነበረው ደመወዝ ለተሾመበት ደረጃ ከተወሰነው መነሻ ደመወዝ በታች ከሆነ ለደረጃው የተወሰነውን የመነሻ ደመወዝ ያገኛል፤

፪· ሆኖም ከመሾሙ በፊት ሲያገኝ የነበረው ደመወዝ ለተሾመበት ደረጃ ከተወሰነው የመነሻ ደመወዝ በላይ ወይም እኩል የሆነ እንደሆነ አዲስ ደመወዙ ከመሾሙ በፊት ያገኝ ከነበረው ደመወዝ ቀጥሎ ባለው የእርከን ደመወዝ ላይ ይሆናል።

## Section Three
## *Transfer*

27. *Principle*

A prosecutor may be transferred from place to place or from one job to another by the Ministry or upon the requests of the prosecutor for such transfer.

28. *Troansfer of Prosecutor by the Ministry*

1) The Ministry may transfer a prosecutor from one place to another or from one job to another when necessary and for the expeditious execution of the work, taking into account the work load and biligence of the prosecutor provided that the prosecutor's benefits are not negatively affected.
2) Transfer of prosecutors by the Ministery referred to in sub article 1 of this Article shall be carried out on the basis of a study by the higher commission and , as much as possible, according to plan.

29. *Transfer on Application*

1) Application for transfer by a prosecutor shall be made in writing to the higher commission through the Ministry's Adminsitrative and Finance Department.
2) The higher commission shall examine the application for transfer and submit its opinion to the minster. The higher commission may seek the opinion of the superior of the prosecutor requesting the transfer before giving its opinion to the minister. The decision of the minsiter shall be final.
3) Unless authorized by the minsiter on the ground of health problem or for any other convincing reason, a prosecutor shall serve at least for two years in the place where he has been assigned before applying for transfer.

## Section Four
## *Salary*

30. *Salary Scale*

Salaries payable to prosecutor assigned or appointed at different grades shall be in accordance with the salary scale of the Federal prosecutors formulated by the Ministry.

31. *Starting Rate*

A newly assigned prosecutor shall be paid the starting rate of the grade he is assigned to.

32. *Starting Rate For Appointment*

1) Where a prosecutor is appointed, he shall receive a starting salary of the grade he has been appointed to if the salary he was receiving before his appointment is less than the starting salary of the new grade.
2) Where the salary he was receiving before his appointment is more than or equal to the starting salary of the new grade his new salary shall be the one specified at the next higher step.

፴፫· በደረጃ ተመሳሳይ ወደሆነ ሥራ ስለመዛወር

አንድ ዐቃቤ ሕግ ከያዘው ሥራ ተመሳሳይ ወደሆነ ሌላ ሥራ ሲዛወር ወይም ሲመደብ ደመወዙና ደረጃው ቀድሞ የነበረው ይሆናል።

፴፬· ከፍ ወዳለ የሥራ ደረጃ በጊዜያዊነት ስለመመደብ

፩· አንድ ዐቃቤ ሕግ ከፍ ወዳለ የሥራ ደረጃ በጊዜያዊነት ወይም በተተኪነት ሲመደብ ደመወዙ ቀድሞ ሲያገኝ ከነበረው አይለወጥም

፪· አንድ ዐቃቤ ሕግ ከፍ ወዳለ የሥራ መደብ በጊዜያዊነት ወይም በተተኪነት ተመድቦ መቆየት የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ነው።

፴፭· ከደረጃ ዝቅ ስለማለት

አንድ ዐቃቤ ሕግ በዲስፕሊን ጥፋት ወይም የሥራ አፈጻጸሙ አጥጋቢ ባለመሆኑ ከደረጃው ዝቅ እንዲል ዋናው ጉባዔ ሲወስን ደመወዙ እንደነገሩ ሁኔታ ዐቃቤ ሕጉ ዝቅ ባለበት ደረጃ መነሻ ደመወዝ ወይም ከመነሻው ደመወዝ ቀጥሎ ባለ በማናቸውም የእርከን ደመወዝ ላይ ይመደባል።

፴፮· በየጊዜው ስለሚደረግ የእርከን ደመወዝ ጭማሪ

፩· በዚህ ደንብ ውስጥ በሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ዐቃቤ ሕግ ለያዘው ደረጃ በደመወዝ ስኬል ውስጥ የተመለከተውን የእርከን ጭማሪ በየሁለት ዓመት የሚያገኘው፣
   ሀ) በሥራ አፈጻጸሙና በሥነ ምግባሩ አጥጋቢ ሆኖ ሲገኝ፣
   ለ) ደመወዙ ለደረጃው ከተወሰነው ጣሪያ ያላለፈ እንደሆነ ነው።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረገው የደመወዝ ጭማሪ መጠን የጭማሪ ውሣኔ ከመደረጉ በፊት ዐቃቤ ሕጉ ሲያገኝ በነበረው ደመወዝና ቀጥሎ በሚገኘው የእርከን ደመወዝ መካከል ያለው ልዩነት ይሆናል።

፴፯· ስለእርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜ አቆጣጠር

በዚህ ደንብ መሠረት በየሁለት ዓመት የሚሰጥ የእርከን ደመወዝ ጨማሪ የመቆያ ጊዜ የሚቆጠረው ዐቃቤ ሕጉ ከተሾመበት ወይም የመጨረሻውን ጭማሪ ካገኘበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

፴፰· ሹመት በእርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜ ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አንድ ዐቃቤ ሕግ በሹመት ምክንያት የሚያገኘው ደመወዝ ባይሾም ኖሮ በሚቀጥለው የጭማሪ ጊዜ ማግኘት ከሚችለው የእርከን ደመወዝ እኩል የሆነ እንደሆነ፣ የሚቀጥለው የእርከን ጨማሪ መቆያ ጊዜው ከሹመቱ በፊት ጭማሪ ከአገኘበት ቀን ጀምሮ ይቆጠራል።

፴፱· ከደረጃ ዝቅ ማለት በእርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜ ላይ ስለሚኖረው ውጤት

በዲስፕሊን ጥፋት ወይም የሥራ አፈጻጸሙ አጥጋቢ ባለመሆኑ አንድ ዐቃቤ ሕግ ቀደም ሲል ከያዘው ደረጃ ዝቅ የተደረገ እንደሆነ የእርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜው በደረጃ ዝቅ ካለበት ቀን ጀምሮ ይቆጠራል።

፵· የደመወዝ ጭማሪ አፈጻጸም

የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ለዐቃቤያነ ሕግ የሚጠየቀውን የደመወዝ ጭማሪ ከዓመት በጀቱ ጋር ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል።

33. *Transfer to work of equal position*

Where a prosecutor is transferred or assigned to another work of a similar nautre, his salary and position shall remain the same.

34. *Temporary Assignment to a Higher Position*

1) The salary of a prosecutor assigned, temporarily or as a substitute, to higher position shall remain the same.
2) A prosecutor may be assigned temporarily or as a substitute to a higher position for six (6) months only.

35. *Demotion*

Where a prosecutor is demoted by the higher commission for disciplinary offence or inefficiency, his salary may, as the case may be, the starting rate or any salary next to the starting rate of position he is demoted to.

36. *Preiodic Salary Increments*

1) Without prejudice to other provisions of these Regulations a prosecutor shall be entitled to periodic increment of salary referred to in the salary scale every two years where:
   (a) his performance and conduct has been satisfactory,
   (b) it does not exceed the maximum salry of his grade.
2) The increment referred to in sub article 1 of this Aritcle is the differece in amount between the salary that the prosecutor has been receiving before a decision to give increment and the next step.

37 *Calculation of Increment Waiting Period*

The two year waiting period for salary increment in accordance with these Regulations shall commence running from the date of appointment of the prosecutor or last increment he was granted.

38. *Effects of appointment on Increment waiting Period*

Where the salary of a prosecutor as a result of his appointment to a higher grade is equal to that of the next step salary for whcih he would have been eligible had he not been appointed, the waiting period for the next periodic increment shall continue to run from the date of the last periodic increment in the grade from which he was appointed.

39. *Effects of demotion on Increment Waiting Periodes*

*Where a prosecutor is demoted for reasons of disciplinary breach or inefficiency, the waiting period shall begin to run as of the effective date of such demotion.*

40. *Execution of Sarlary increment*

The Ministry shall submit to the Ministry of Finance its request for periodic increment for prosecutors together with its annual budget.

፵፩· ስለደመወዝ አከፋፈልና ደመወዝን በቅድሚያ ስለመክፈል

፩· የዓቃብያነ ሕግ ደመወዝ የሚከፈለው በየወሩ ከሃያ ስድስተኛው ቀን አንስቶ እስከ ወሩ የመጨረሻ ቀን ይሆናል።

፪· አንድ ዐቃቤ ሕግ ደመወዙ በቅድሚያ እንዲከፈለው መብት፡ አይደለም፡ ሆኖም ዐቃቤ ሕጉ የዓመት ፈቃድ የወጣ ከሆነ ፈቃድ ለወጣበት ወር ደመወዙ በቅድሚያ ይከፈለዋል።

፵፪· ስለልዩ ልዩ አበሎች

ለማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የሚከፈል ማናቸውም ዓይነት አበል በተለይ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

## ንዑስ ክፍል አምስት
## ስለሕክምናና የጉዳት ካሣ

፵፫· በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት በመጣ ሕመም ስለሚከፈል የጉዳት ካሣ

፩· በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት በመጣ ሕመም ዘላቂና ሙሉ የአካል ጉዳት ደርሶበት ሥራ መሥራት የማይችል ዐቃቤ ሕግ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት መብቱ ይከበርለታል።

፪· አንድ ዐቃቤ ሕግ በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ወይም በመጣ ሕመም ዘላቂ የሆነ ከፊል የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነና የደረሰውም ጉዳት ሥራውን ሙሉ በሙሉ እንዲያቋርጥ የማያስገድደው ሲሆን ሥራውን የሚቀጥል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለደረሰት የአካል ጉዳት አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት ካሣ ይከፈለዋል።

፵፬· የሕክምና አገልግሎት ስለማግኘት

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሲታመም የሕክምና ወጭው ሙሉ በሙሉ በመሥሪያ ቤቱ እየተሸፈነለት በተመላላሽም ሆነ በሆስፒታል ተኝቶ የመታከም መብት ይኖረዋል።

፪· የዐቃቤ ሕግ ሚስት፣ ባል ወይም ልጅ ሲታመም የሕክምና ወጭ ግማሽ በመሥሪያ ቤቱ እየተሸፈነለት በተመላላሽም ሆነ ሆስፒታል ተኝቶ የመታከም መብት ይኖረዋል።

፫· መሥሪያ ቤቱ ዐቃብያነ ሕግ ሊታከሙ የሚችሉባቸውን መንግሥታዊ የሕክምና ተቋማት ሊመርጥ ወይም ሊወስን ይችላል።

## ንዑስ ክፍል ስድስት
## ስለዐቃብያነ ሕግ ስለሚቀርብ ዘገባ

፵፭· ስለዐቃብያነ ሕግ የሥራ አፈጻጸም ዘገባ

፩· እያንዳንዱ የበላይ ዐቃቤ ሕግ የሚቆጣጠራቸውን ዐቃብያነ ሕግ የሥራ አፈጻጸም በአግባቡ በመከታተልና በመገምገም በየዓመቱ ታኅሣሥ ፴ ና ሰኔ ፴ ቀን ዘገባ አዘጋጅቶ ያቀርባል። ዘገባው የሚቀርብለት የበላይ ዐቃቤ ሕግም በዘገባው ላይ በተጨማሪ እንዲፈርምበት ያስፈልጋል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስትሩ በማናቸውም ጊዜ ስለማናቸውም ዐቃቤ ሕግ ዘገባ እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል።

41. *Mode of payment and Payment in Advance*

1) The salary of prosecutors shall be paid every month starting from the 26th to the final day of the month.
2) A prosecutor is not entitled to the payment of salary in advance. In case of leave however, the salary of a prosecutor shall be paid in advance for the leave month.

42. *Allowances*

Any allowance payable to a prosecutor shall be determined by special directives.

## Section Five
## *Medical Benefits and Damages*

43. *Damages in case of Employment injuries or occupational disease*

1) The right of a prosecutor permanently and totally disabled due to employment injury or occupational disease, shall be realised in accordance witht he relevant pension law.
2) Where a prosecutor has suffered permanent and partial disablement caused by employment injury or occupational disease, but is still fit for work, he shall continue in his work. He shall, however, be entitled to compensation in accordance with the relevant pension law.

44. *Medical Benefits*

1) A prosecutor shall have the right during his sickness, to be treated in a hospital as an in-patient or out-patient and the full medical expenses shall be covered by the Ministry.
2) Where the spouse or the children of prosecutor are sick they shall have the right, during their sickness, to be treated in a hospital as an in-patient or out–patient and half of the medical expense shall be covered by the Ministry.
3) The Ministry may select or designate government medical institutions where prosecturors may be treated.

## Section Six
## *Reports Concerning Prosecutors*

45. *Prosecutors Efficiency Reports*

1) Every superior prosecutor shall supervise and evaluate the performance of prosecutors under his supervision and submit efficiency report every year by the end of the months of Tahsas and Sene. The superior prosecutor who receives the report shall countersign it.
2) Without prejudice to sub Article (1) of this Article the minister may require report about any prosecutor at any time.

፵፮· በሙከራ ላይ ስላለ ዐቃቤ ሕግ ስለሚቀርብ ዘገባ

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫ በተመለከተው መሠረት በሙከራ ላይ ስላለ ዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈጻጸም የሚዘጋጅ የመጀመሪያ ዘገባ ዐቃቤ ሕጉ ከተቀጠረበት ቀን አንስቶ የሚታሰብ የዘጠና (፺) ቀናት ጊዜ እንዳለቀ መቅረብ አለበት። ሁለተኛው ዘገባ ደግሞ የሙከራ ጊዜው ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት።

፪· የሙከራ ጊዜው የተራዘመ እንደሆነ የተራዘመው ጊዜ ከማለቁ አሥራ አምስት ቀናት አስቀድሞ ለሙከራ ስለተቀጠረው ዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈጻጸም ዘገባ መቅረብ አለበት።

፵፯· ስለሥራ አፈጻጸም ዘገባዎች አያያዝ

፩· ስለዐቃብያነ ሕግ የሥራ አፈጻጸም የሚቀርቡ ዘገባዎች ሁሉ በዐቃቤ ሕጉ የግል ማኅደር ውስጥ ተያይዘው መቀመጥ አለባቸው።

፪· በዚህ ደንብ መሠረት በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ የዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈጻጸም ዘገባ በምስጢር መጠበቅ አለበት።

፵፰· ስለሥራ አፈጻጸም ጉድለት የሚቀርቡ ዘገባዎች

፩· ስለአንድ ዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈጻጸም በቀረበው ዘገባ ዐቃቤ ሕጉ ያገኘው ማዕከላዊ ውጤት ዝቅተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ ዘገባ አቅራቢው ዐቃቤ ሕግ ወይም ባለሥልጣን ስለዘገባው ከሚመለከቻው ዐቃቤ ሕግ ጋር መነጋገር አለበት። የሥራ አፈጻጸም ዘገባ የቀረበበት ዐቃቤ ሕግም ስለዘገባው ያለውን አስተያየት በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል። ዐቃቤ ሕጉ የሚሰጠው አስተያየት ከዘገባው ጋር በግል ማኅደሩ ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ አለበት።

፪· በተሞላው የሥራ አፈጻጸም ውጤት ላይ የሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ ቅሬታ ያለው ከሆነ የሥራ አፈጻጸሙን የሞላው ሐላፊና የእርሱ የበላይ ጉዳዩን በጋራ እንዲያዩት መደረግ አለበት። የበላይ ኃላፊው የደረሰበት ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፵፱· ስለችሎታ ማነስ የሚቀርብ ዘገባ

ማንኛውም በቋሚነት የተቀጠረ ዐቃቤ ሕግ ችሎታው እጅግ ዝቅ ያለ ከመሆኑ የተነሳ ከሥራ የመሰናበት ውሣኔ የሚሰጥበት ሁኔታ ሲኖር ዘገባ አቅራቢው በዘገባው ላይ "የችሎታ ማነስ" የሚል ምልክት ያደርግበታል።

ንዑስ ክፍል ሰባት

ስለአቤቱታ

፶· መሠረታዊ ሃሣብ

ማናቸውም ዐቃቤ ሕግ ስለሚደርስበት በደል አቤቱታ ለማቅረብ መብት አለው። ሆኖም አቤቱታውን ለማቅረብ የሚችለው በደሉ ተፈጸመብኝ ከሚልበት ጊዜ ጀምሮ ቢያንስ ፳፬ ሰዓት ካለፈ በኋላ ነው። አቤቱታው በጽሑፍ ሆኖ ለአቤት ባዩ ዐቃቤ ሕግ የቅርብ ኃላፊ መቅረብ አለበት።

፶፩· አቤቱታን ስለማጣራትና ውሣኔ ስለመስጠት

፩· አቤቱታ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በአሥር /፲/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢ ውሣኔ ወይም ምላሽ መስጠት አለበት።

46. *Efficiency Report During Probation*

1) The first efficiency report about a prosecutor on probation referred to in Article 13 of these Regual-tions shall be submitted ninety (90) days after his employment The next report shall be made one month before the completion of the probation period.

2) Where the probation period is extended, efficiency report shall be submitted fifteeen days before the expiry of the extended period of probation.

47. *Maintenance of Efficiency Reports*

1) All efficiency reports shall be kept in the personal file of the prosecutor concerned.

2) Efficiency reports of a prosecutor submitted at any time under these Regulations shall be kept confidentially.

48. *Inefficiency Reports*

1) Where the efficiency report of a prosecutor is below averge, the reporting prosecutor or official, shall discuss the report with the concerned prosecutor. The prosecutor about whom the report has been submitted may gove remarks in writing on the report and the remarks shall be filed in the personal file together with the report concerned.

2) Where a prosecutor has objections on the efficiency report, the reporting official and his superior shall see the case together. The decision of the superior shall be final.

49. *Adverse Reports*

In case where the efficiency of a permanently employed prosecutor is extremely low to warrant his dismissal, the reporting official shall mark on the report "adverse report."

Section Seven

*Complaints*

50. *Principles*

Every prosecutor shall have the right to complain if he is aggrieved; However, such complaint may not be lodged before at least twenty-four (24) hours have elapsed since the incident occurred. Complaints shalll be made in writing to the immediate superior of the prosecutor who lodges the complaint.

51. *Investigation and Decision on the Complaint*

1) The superior shall give appropriate decision or response within ten (10) working days upon receiveing the complaint.

፪· አቤቱታ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፩ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢ ውሣኔ ወይም ምላሽ ያልሰጠበት እንደሆነ ወይም አቤት ባዩ ዐቃቤ ሕግ በውሣኔው ያልተስማማበት ከሆነ ጉዳዩን ለሚኒስትሩ ለማቅረብና ለማሰማት ይችላል። ሚኒስትሩ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፫· አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስትሩ ስለአቤቱታው ደንበኛ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዝ ይችላል።

## ንዑስ ክፍል ስምንት
## ስለሥልጠና

### ፶፪· ስለሥልጠና ፕሮግራም

መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት እና የሚቀይሳቸውን ዓላማዎች ማሳካት ይችል ዘንድ፣

፩· በቅጥር ወይም በዝውውር አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት አዲስ የሚቀጠሩ ዐቃብያነ ሕግ ስለመሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት፣ ፖሊሲዎችና የአፈጻጸም ሥርዓቶች፣ የአሠራር ልማዶችን ደንቦች እንዲሁም ስለሚመደቡበት ሥራ አጠቃላይ እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ መሥሪያ ቤቱንና የሥራ አካባቢያቸውን እንዲያውቁና እንዲለምዱ የሚያግዝ የመተዋወቂያ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣

፪· ዐቃብያነ ሕግ በተመደቡበት ሥራ ውጤታማና ቀልጣፋ ይሆኑ ዘንድ በየጊዜው የሚፈጠሩ አዳዲስ የሙያ ዕውቀቶችን እንዲሁም የአሠራርና የግንኙነት ዘዴዎችን በመቅሰምና የልምድ ልውውጥ በማድረግ የሙያ ዕውቀታቸውን እንዲያጎለብቱ፣ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን እንዲያሰፉና በተጨማሪም በኃላፊነት ደረጃ የተመደቡት የአመራር ብቃታቸውን ለማጎልበት እንዲችሉ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የሥልጠና ፕሮግራም ያቀዳል፣ ያስፈጽማል።

### ፶፫· ስለሥልጠና ፕሮግራም አፈጻጸም

፩· መሥሪያ ቤቱ ለአዲስ ተቀጣሪ ዐቃብያነ ሕግ የሚያዘጋጀው የመተዋወቂያ ፕሮግራም በሚኒስቴሩ ይከናወናል።

፪· ሚኒስቴሩ ዐቃብያነ ሕግን ለማሠልጠን የሚያዘጋጀው የሰው ኃይል ሥልጠና ፕሮግራም እንደ ሁኔታው ሚኒስቴሩ በሚያቋቁመው የማሠልጠኛ ተቋም ወይም በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በሚገኙና አግባብ ካላቸው ተቋሞች ሙሉ በሙሉ ወይም በትብብር ሊከናወን ይችላል።

### ፶፬· ስለሰልጣኝ ዐቃቢያነ ሕግ ግዴታ

ማንኛውም ዓቃቤ ሕግ፣

፩· ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው አግባብ ባለው የሥልጠና ፕሮግራም በሙሉ ፈቃደኝነት የመሳተፍ፣

፪· በመሥሪያ ቤቱ ውሣኔ ለሥልጠና የተላከበትን የሥልጠና ዘርፍ ወይም የሙያ መስክ ለመቀየር፣ ለማቋረጥ ወይም ለማራዘም ሲፈልግ መሥሪያ ቤቱን በቅድሚያ የማስፈቀድ፣

፫· በመሥሪያ ቤቱ ድጋፍ ሥልጠና ባገኘበት ሙያ ቢያንስ ሥልጠናው በወሰደው ጊዜ ልክ ሁለት እጥፍ ለሆነ ጊዜ ለመሥሪያ ቤቱ አገልግሎት የማበርከት ግዴታ አለበት።

2) If the superior does not give appropriate decision or response on the complaint within the time limit referred to in sub-Article 1 of this Article, or if the complainant disagrees over the decision, he has the right to submit the complaint to the minister. The decision of the Minister shall be final.

3) Where necessary, the Minister may order formal investigation of the complaint.

## *Section Eight*
## *Training*

### 52. *Training Schemes*

To accomplish its responsibilities efficiently and achieve its objectives, the Ministry shall:

1) Prepare orientation programs for new entrants to familiarize them with the working enivronment, the structure, policies, the nature of the work and working procedure of the Ministry.

2) design and execute training programs that enhance efficiency through training on new idea and practice and through exchange of experience, thus increasing their professional knowledge and horizon as well as design and execute training programs that develop leadership capabilities of those with supervisory responsibilities.

### 53. *Training Procedure*

1) Orientation programs for new recruits shall be conducted by the Ministry.

2) Training programs prepared by the Ministry for human resource development may be conducted in an institution established by the Ministry, in other appropriate institutions, locally or abroad, or in collaboration with these institutions, as the case may be.

### 54. *Obligation of Trainee Prosecutor*

Any prosecutor shall:

1) Participate with full consent in the appropriate training program designed by the Ministry;

2) Obtain the prior permission of Ministry where he desires to change, cease or extend the field of training for which the Ministry has sent him;

3) Serve the Ministry for at least twice the period of his training in the field he has been trained with the support of the Ministry.

## ክፍል አራት
## አገልግሎት ስለማቋረጥ

### ፶፭· ሥራን በገዛ ፈቃድ ስለመልቀቅ

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም ጊዜ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመተው ይችላል።

፪· ሥራን በገዛ ፈቃድ ለመልቀቅ የሚቀርበው ጥያቄ ዐቃቤ ሕጉ ሥራውን ለማቆም ከሚፈልግበት ቀን አንድ ወር አስቀድሞ በጽሑፍ መቅረብ አለበት።

፫· ሥራ ይበደላል ተብሎ የሚታመን ሲሆን ዐቃቤ ሕጉ ሥራውን ለማቆም የሚፈልግበትን ቀን ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘም ሚኒስትሩ መወሰን ይችላል።

፬· አንድ ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም ምክንያት መሥሪያ ቤቱን ሲለቅ የአገልግሎቱን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃና የምሥክር ወረቀት የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

፭· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ጥያቄ ሲቀርብ በሚሰጠው የሥራ መልቀቂያ የምሥክር ወረቀት ላይ የሚከተሉት መገለጽ ይኖርባቸዋል፤

ሀ) የአገልግሎት ዘመን የተጀመረበትንና የተቋረጠበትን ቀን፣

ለ) ሥራውን የለቀቀበት ምክንያት፤

ሐ) በአገልግሎቱ ዘመን የሥራ አፈጻጸሙ ግምገማ ውጤት ምን እንደሚመስል በጉልህ የሚገልጹ መረጃዎች፣

መ) ዓቃቤ ሕጉ በአገልግሎቱ ዘመን በየጊዜው የያዘው የሥራ መደብና ደረጃው ከነደመወዙ።

### ፶፮· በመጦሪያ ዕድሜ ገደብ ምክንያት አገልግሎት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

፩· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዐቃብያነ ሕግ በጡረታ ከሥራ የሚገለሉበት ዕድሜ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ የተወሰነው ይሆናል።

፪· በዕድሜና ዕድሜ ሣይደርስ ጡረታ የሚወጡ ዐቃብያነ ሕግ መብትና ግዴታ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ በተወሰነው መሠረት ይፈጸማል።

፫· አንድ ዐቃቤ ሕግ ስለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አገልግሎት በሕግ የተወሰነው የዕድሜ ገደብ ከሚፈጽምበት የመጨረሻ ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ያለተጨማሪ ሥነ ሥርዓት ሥራውን እንዲያቆም ይደረጋል።

፬· ዐቃቤ ሕጉ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ምክንያት ሥራውን የሚያቆምበትን ቀን ከሶስት ወር አስቀድሞ በጽሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል።

፭· አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ሲፈቀድ አንድ ዐቃቤ ሕግ በዕድሜ ገደብ ምክንያት ለመንግሥት የሚያበረክተውን አገልግሎት ማቋረጥ ከሚገባው ዕድሜ (፭) ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በሥራው ላይ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል።

፮· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተደነገገው መሠረት አንድ ዐቃቤ ሕግ በሕግ የተወሰነውን የዕድሜ ገደብ ከፈጸመ በኋላ በሥራው ላይ እንዲቆይ የሚደረገው ዐቃቤ ሕጉ ለሥራው እጅግ ጠቃሚ ሲሆንና ለሥራው የተወሰኑትን የሥራ ግዴታዎችንና ተፈላጊ የጤና ሁኔታዎችን አሟልቶ ሲገኝና በሥራው ላይ ለመቆየት ሲስማማበት ነው።

### ፶፯· በሕመም ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከሕመሙ የመዳን ተስፋ የሌለው ዐቃቤ ሕግ ሥራውን እንዲተው ይደረጋል።

## PART FOUR
## *Termination of Service*

### 55. *Resignation*

1) A prosecutor may resign from service at any time.
2) Notification of resignation shall be given in writing at least one (1) month before the resignation is to take effect.
3) The effective date of the resignation may be postponed by the Minister for no longer than one month if the resignation of the prosecutor is believed to negatively affect the work.
4) A prosecutr who resigns from the ministry for whatever reason has the right to request and receive a certificate indicating conditions of his service.
5) The certificate requested under sub Article 4 of this Article shall indicate the following:
   (a) date of commencement and termination of service;
   (b) the reason for resignation;
   (c) clear indications of the results of efficiency reports during his tenure of service;
   (d) the rank and position he has been assigned and the salary he was receiving during his tenure of service.

### 56. *Retirement*

1) Without prejudice to sub Article 5 of this Article, retirement age of a prosecutor shall be determined in acccordance with Federal Public service Pension law.
2) The right and duties of a prosecutor retiring on or before retirement age shall be in accordance with Federal Public Service Pension law.
3) The retirement of a prosecutor shall become effective on the last day of the month in which he attains retirement age without special procedure.
4) A prosecutor retiring for the reason stated under sub Article 1 of this Article shall be informed of the retirement in writing three (3) months prior to the date of this retirement.
5) A prosecutor may be retained in service beyond the retirement age for a period not exceeding five (5) years with the approval of the appropriate government organ.
6) A prosecutor may be retained in service beyond retirement age as provided in sub Article 5 of this Article only if he is extremely useful for the work and still fulfills the medical and other conditions of service and agrees to a retention in service.

### 57. *Retirement Due to Sickness*

1) without prejudice to Article 20 of these Regulations, a prosecutor shall be retired if there is no prosepect of early recovery.

፪· በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፳ መሠረት የሚወሰደው የሕመም ፈቃድ በአራት ዓመት ውስጥ ከስምንት (፰) ወር የበለጠ ሆኖ ሲገኝ፣ ከዚያ ወዲያ ዐቃቤ ሕጉ ለተመደበበት ሥራ እንደማይገባ ሆኖ ይገማታል። ይህም ሲሆን ሚኒስትሩ ከስምንተኛው ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ዐቃቤ ሕጉ ከሥራው እንዲሰናበት ማዘዝ ይችላል።

፶፰· ዐቃብያነ ሕግ የተመደቡበት የሥራ ዘርፍ በመሠረዙ ምክንያት ስለሚደርስ የአገልግሎት መቋረጥ

፩· አንድ ዐቃቤ ሕግ ተመድቦበት የነበረው ሥራ የተሠረዘ እንደሆነ በነበረው ደረጃ ወደ ሌላ ሥራ ተዛውሮ እንዲሠራ መደረግ አለበት።

፪· ዐቃቤ ሕጉን በሶስት ወር ውስጥ ወደሌላ ሥራ ለማዛወር ያልተቻለ እንደሆነ በሕግ የተወሰኑት ሌሎች መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ አስቀድሞ የ፩ ወር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ከሥራው ይሰናበታል።

፶፱· የሥራ ችሎታ ያነሰውን ዐቃቤ ሕግ ከሥራ ስለማሰናበት

፩· አንድ ዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ሆኖ ከተገኘ በሚቀርበው ዘገባ መሠረት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ከሥራ ይሠናበታል።

፷· እሥራት የተፈረደበትን ዐቃቤ ሕግ ከሥራ ስለማሰናበት

፩· አንድ ዐቃቤ ሕግ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የመጨረሻ በሆነ ፍርድ ከአንድ ዓመት ያላነሰ እሥራት የተፈረደበት እድሆነ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ ከሥራ እንደተወገደ ይቆጠራል። ይህ በሆነ ጊዜ ዐቃቤ ሕጉ ከሥራው የተወገደ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ እንዲደርሰው መደረግ አለበት።

## ክፍል አምስት
## ስለዐቃብያነ ሕግ ግዴታ

፷፩· ስለታማኝነት

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ መላ ጉልበቱንና ችሎታውን በታማኝነት ለመንግሥትና ለሕዝብ አገልግሎት ጥቅም ማዋል አለበት።

፷፪· ስለእያንዳንዱ ዐቃቤ ሕግ ጠባይ

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የሕዝብን አክብሮትና እምነት እንዲያገኝ በመሥሪያ ቤቱም ሆነ ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ በማናቸውም ጊዜ መልካም ጠባይና ሥነ ምግባር እንዲኖረው ያስፈልጋል።

፪· በማንኛውም ጊዜ የሙያውን ክብር ለማስጠበቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟልቶ መገኘት አለበት።

፷፫· ስለታዛዥነት

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ፣ ሥራውን ባለው ከፍተኛ ዕውቀትና ችሎታ መፈጸም አለበት ፣ የተመደበበትን መደበኛ ሥራና ሌላውንም ተመሣሣይ ሥራ መፈጸም ግዴታው ነው።

፪· ዐቃቤ ሕጉ ከበላይ ኃላፊው የሚሰጠው ትዕዛዝ በግልጽ ከሕግ ውጭ ካልሆነ በቀር እንደትዕዛዙ መፈጸም አለበት። በማናቸውም አኳኋን የበላይ ዐቃቤ ሕግ ለሚሰጠው ትዕዛዝ ሕጋዊነት ኃላፊ ነው።

፷፬· ዐቃቤ ሕግ ከሕዝብ ጋር ስላለው ግንኙነት

፩· ዐቃቤ ሕግ የሚፈጽማቸው ተግባሮች በጠቅላላው የመላውን ሕዝብ ጥቅም የሚመለከቱ መሆናቸውን ምን ጊዜም መዘንጋት የለበትም።

፪· ዐቃቤ ሕግ የሰዎችን ሰብአዊ መብትና ክብር መንካት የለበትም።

2) Where the sick leave taken pursuant to Article 20 of these Regulations exceeds eight (8) months within four (4) years, it shall be presumed that the prosecutor is no longer fit for service. In such a case the Minister may order that the retirement be effctive on the last day of the 8th month.

58. *Retirement Due to Cancellation of Position*

1) Where the position to which a prosecutor was assigned is cancelled, he shall be transferred to another job retaining his previous position.
2) Without prejudice to the rights of the prosecutor under other relevant laws, where the transfer cannot be made within three (3) months, he shall be retired upon being given one (1) month prior notice.

59. *Dismissal on Grounds of inefficiency*

A prosecutor may, on the basis of the report, be dismissed on grounds of inefficiency on one (1) month prior notice.

60. *Dismissal on Grounds of Conviction*

A prosecutor shall be deemed dismissed without notice if he is sentenced to a term of not less than one year imprisonment on the basis of a final judgment by a court of competent jurisdiction. A letter confirming the fact of his dismissal shall be duly sent to him.

## *PART FIVE*
## *Obligation of Prosecutors*

61. *Loyalty*

Any prosecutor shall devote his whole energy and ability to providing loyal service in the interest and for the benefit of the government and the public.

62. *Personal Conduct of a Prosecutor*

1) Any prosecutor shall at all times exhibit good behavior and conduct within and outside the office in order to win the respect and confidence of the public.
2) He shall, at all times, fulfill whatsoever required of him to protect the dignity of his profession.

63. *Obedience*

1) Any prosecutor shall perform his duties to his best knowledge and ability. He is required to discharge the usual duties and other related duties of the grade and the position to which he has been appointed and other related duties.
2) A prosecutor shall obey the orders of his superior unless it is clearly contrary to the law. In all cases the superior is responsible for the legality of his orders.

64. *Prosecutor's Relations with the Public*

1) A prosecutor shall always bear in mind that his actions concern the interest of the public.
2) A prosecutor shall respect human rights and human dignity.

፷፭· <u>ምስጢር ስለመጠበቅ</u>

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ፡

፩· መረጃው ተራ ወይም በሕዝብ ዘንድ የታወቀ ካልሆነ ወይም መደበኛ ሥራውን በሕጋዊ መንገድ ለመፈጸም አስፈላጊ ካልሆነ በቀር በሥራው አጋጣሚ ወይም ምክንያት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘውን መረጃ ለማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም።

፪· ሥልጣን ባለው ኃላፊ በአግባቡ ካልታዘዘ በቀር በአሠራር ምስጢር የተባሉትን መረጃዎች፣ ቃለ ጉባዔዎች፣ የሥራ ዕቅዶችና እነዚህን የመሳሰሉትን ምስጢራዊ ጉዳዮች ሁሉ በሥራም ላይ ሆነ ከሥራ ውጭ ጉዳዩን እንዲያውቀው በደንቡ ለተፈቀደለት ሰው ካልሆነ በቀር ለሌላ ማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም።

፷፮· <u>ገንዘብ ስለመበደር</u>

፩· አዘውትሮ ገንዘብ መበደር ክልክል ነው።

፪· ዐቃቤ ሕግ በሥራው ምክንያት ከሚያጋጥመው ማናቸውም ሰው ገንዘብ መበደር ወይም ለመበደር መሞከር ፍጹም ክልክል ነው።

፷፯· <u>ስጦታዎች</u>

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስለ ሰጠው ወይም ወደፊት ስለሚሰጠው አገልግሎት ከማና ቸውም ሰው ማናቸውም ዓይነት ስጦታ ወይም ዋጋ መጠየቅ ወይም መቀበል የለበትም።

፷፰· <u>በመንግሥት ሥራና በግል ጉዳዮች ወይም ጥቅሞች መካከል ስለሚፈጠር ግጭት</u>

፩· ማናቸውም ዐቃቤ ሕግ የራሱ፣ የዘመዶቹ ወይም የወዳጆቹ የግል ጉዳይ ወይም ጥቅም ከሥራው ወይም በሥራው ምክንያት ከያዘው የሕዝብ ወይም የግለሰብ ጉዳይ ጋር የሚጋጭ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ችግር ለበላይ ኃላፊው ወዲያውኑ በማሳወቅ ጉዳዩ በሌላ ዐቃቤ ሕግ እንዲታይ ማመልከት አለበት።

፪· ጉዳዩ የቀረበለት የበላይ ዐቃቤ ሕግም አስፈላጊ የመሰለውን ውሣኔ መስጠት አለበት።

፷፱· <u>ስለግል ደብዳቤዎች</u>

፩· ዐቃብያነ ሕግ በመሥሪያ ቤቱ አድራሻ የግል ደብዳቤ ሊጽፉ ወይም ከሌላ ሊጻፍላቸው ይችላል ። ስለዚሁ ጉዳይ የሚያስፈልገውን የመላላክ ወጪ ጉዳዩ የሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ መክፈል አለበት ።

፪· በመሥሪያ ቤቱ አድራሻ የተላከ የማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ደብዳቤ፣ ጥቅል ወይም ዕቃ ቢጠፋ መሥሪያ ቤቱ በኃላፊነት አይጠየቅም።

፸· <u>በመሥሪያ ቤቱ መገልገያዎች ስለመጠቀም</u>

ዐቃቤያነ ሕግ ሥራቸውን በሚገባ ለመፈጸም ያህል ብቻ በመሥሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ መገልገያዎች ለመጠቀም ይችላሉ ።

፸፩· <u>ለሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ስለ መሥራት</u>

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ

ሀ) በመደበኛ የሥራ ሰዓት መላ ጉልበቱን ፡ ችሎታውንና አሳቡን በደመወዝ በተመደበበት የመሥሪያ ቤቱ ሥራ ላይ ማዋል አለበት ። ሆኖም ዐቃቤ ሕጉ በአግባቡ ሲታዘዝ ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት ልማት ድርጅት መሥራት አለበት ።

ለ) ለመሥሪያ ቤቱ የሚያበረክተውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም ለተሰጠው ሥራና ኃላፊነት ተቃራኒ የሆነ ወይም ከሥራውና ከኃላፊነቱ ወይም ከሙያ ሥነ ምግባር ጋር የማይጣጣም ማናቸውንም የውጭ ሥራ ሊሠራ አይችልም ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የውጭ ሥራ ለመሥራት በቅድሚያ የሚኒስትሩን ፈቃድ ማግኘት አለበት ።

65. *Secrecy*

Any prosecutor:

1) may not disclose to any person any information gained in the course of his official duties or otherwise except to the extent that such disclosure is necessary for the discharge of his lawful duty, unless such information is of minor importance or is a public knowledge.

2) may not disclose in the discharge of his duties or otherwise, information, proceedings, plans or similar classified matters, which, in accordance with practice have been declared confidential, to any person except by the order of supreme authority or unless such other person is legally permitted to know such matters.

66. *Borrowing Money*

1) Persistent borrowing is prohibited.

2) A prosecutor is strictly prohibited from borrowing or attempting to borrow money from a member of the public with whom the prosecutor has a contact in discharge of his official duties.

67. *Gifts*

Any prosecutor may not solicit or take remuneration or consideration in whatever form from any person in respect of services rendered or expected to be rendered.

68. *Conflict of Duty and Private Interest*

1) Any prosecutor shall forthwith report to his superior a case in which his interest or his relative's or friend's interests conflict with his duties and shall request that the case be handled by another prosecutor.

2) The superior shall give the necessary decision.

69. *Private Correspondence*

1) Prosecutors may send or receive private correspondences through the Ministery's address. All expenses arising there from shall be borne by the prosecutor.

2) The Ministry may not be held responsible for the loss of any private letter, parcel or items sent via its address.

70. *Use of Office Equipment*

Prosecutors may utilize office equipment only to the extent necessary to accomplish their work appropriately.

71. *Working for other Government Offices or Private Institutions*

1) Any prosecutor:

(a) Shall during normal working hours, devote his full energy and attention to his official duty for which he is paid. However, a prosecutor shall undertake to work for other governmental offices or public enterprises upon receiving appropriate order.

(b) Shall not undertake any outside activity which would in any way impair his service or which in any way conflicts with his duties or is inconsistent with his position and profession as a prosecutor.

2) Without prejudice to sub Article (1) of this Article, any prosecutor shall obtain prior permission of the Minister to undertake any outside activity.

## ክፍል ስድስት
## የዐቃቤያነ ሕግን የግል ማኅደር ስለማደራጀት

**፸፪· ስለዐቃቤ ሕግ የግል ማኅደርና ካርድ**

፩· መሥሪያ ቤቱ በሥሩ ለሚተዳደረው ለእያንዳንዱ ዐቃቤ ሕግ ማኅደርና የተለየ የግል ካርድ እንዲኖረው ማድረግ አለበት።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት የሚደራጀው የግል ማኅደር ዐቃቤ ሕጉ ሥራ የጠየቀበትን ማመልከቻ ፣ የተቀጠረበትን ደብዳቤ ፣ የትምህርትና የልዩ ሥልጠና ማስረጃ እንዲሁም ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ ለአገለገለበት ዘመን የተሰጠውን የሥራ ምስክር ወረቀት ፣ የደረጃ ዕድገት ወይም ሹመት ያገኘበትን ደብዳቤ ፣ የደመወዝ ጭማሪ የተፈቀደበትን ደብዳቤ ፣ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የጠየቀበትና ያስፈቀደበትን ማመልከቻ የሕመም ፈቃድ ወይም ሌላ ፈቃድ ያገኘበትን ማስረጃ ወይም ጽሑፍ ፣ የሥራ ችሎታና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ፣ በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት የተሰጠ ውሣኔንና እርምጃ የተወሰደበት ጽሑፍ ፣ ከሥራ የተሰናበትበትን ደብዳቤና እነዚህን የመሳሰሉትን ሌሎች መረጃዎች ሁሉ እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ዋናው ቅጂ ወይም ግልባጩን መያዝ አለበት ።

፫· የዐቃቤ ሕጉ የግል ካርድ ከዐቃቤ ሕጉ የግል ማኅደር የተለቀሙ ዋና ዋና ጉዳዮችና መረጃዎች ብቻ የሚመዘገቡበት ይሆናል ።

**፸፫· የግል መረጃዎችን ስለመመርመር**

፩· ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በመሥሪያ ቤቱ በሚገኘው የግል ማኅደሩ ውስጥ የተቀመጡትን መረጃዎች ጠይቆ ለማየትና ለመገልበጥ መብት አለው ።

፪· የመሥሪያ ቤቱ የዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ክፍል ሹም ወይም የዐቃቤያነ ሕግ የግል ማኅደርና ካርድ አከናዋኝ ካልሆነ በቀር በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ወይም ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ የሚገኙ ሌሎች ሰዎች የአንድን ዐቃቤ ሕግ የግል ማኅደር መመርመር የሚችሉት በሚኒስትሩ በጽሑፍ ሲፈቀድ ብቻ ነው ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ለዐቃቤ ሕጉ የተፈቀደውን መብት በመቃረን ወይም በማጓደል ማናቸውንም በዐቃቤ ሕጉ የግል ማኅደር ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ የሚገባውን ማስረጃ ወይም መረጃ ዐቃቤ ሕጉ ሊያያቸው እንደማይችል አድርጎ ማስቀመጥ ወይም ዐቃቤ ሕጉን ለመጉዳት ወይም ለመጥቀም በማሰብ እንዲህ ያለውን ማስረጃ ወይም መረጃ ከዐቃቤ ሕጉ የግል ማኅደር ውስጥ ማውጣት ክልክል ነው ።

፬· በዚህ ደንብ መሠረት ስለዐቃቤ ሕጉ ጤንነት ምርመራ የሚቀርበው ሪፖርት በልዩ ማኅደር እንዲቀመጥ መደረግ አለበት ።

፭· ዐቃቤ ሕጉ ሳያውቀው በግል ማኅደሩ ውስጥ የጽሑፍ ማስረጃ ማስቀመጥ ክልክል ነው ።

## ክፍል ሰባት
## ስለዲስፕሊን
## ንዑስ ክፍል አንድ
## መርህ

**፸፬· ስለዲስፕሊን ቅጣት አላማና አፈጻጸም**

፩· የዲስፕሊን ቅጣት መሠረታዊ ዓላማ ዐቃቤ ሕጉ በፈጸመው ጥፋት ተጸጽቶ እንዲታረምና ወደፊት በብቃት ሥራውን ለማከናወን እንዲችል ለማስተማርና እንዲሁም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማስናበት ነው ።

፪· ሥራውን ችላ የሚል ወይም የማይፈጽም ወይም ማንኛውንም የዲስፕሊን ወይም የሥነ-ምግባር ጉድለት የሚፈጽም ዐቃቤ ሕግ ስለጥፋቱ በፍትሐ ብሔር ሕግና በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተወሰነው መሠረት የሚኖርበት ተጠያቂነት ሳይጓደል በዚህ ደንብ መሠረት የሚወሰኑ ቅጣቶች ይፈጸሙበታል ።

## *PART SIX*
## *Personal Records Of Prosecutors*

72. *Personal File and Personal Card*

1) The Ministry shall keep for any prosecutor a personal file and a separate personal card.
2) The personal file established under sub Article (1) of this Article shall consist of original or copies, as the case may be, of information about the prosecutor related to application for work, the letter of employment, education and special training certificate, certificate of service rendered outside the Ministry, letter of appointment or promotion, notifications of increments of salary, applications and certificates for leave, sick leave or other leave, efficiency reports, letter of disciplinary measures, letter of separation or dismissal and similar information.
3) The personal card of a prosecutor shall contain the most important data and information about the prosecutor.

73. *Examination of Personal Records*

1) Any prosecutor has the right to examine his personal file upon request and to make copies thereof.
2) Persons other than the prosecutors' administration officer and the record clerk for prosecutors, either from within or outside the Ministry, may examine the personal file of a prosecutor only with written permission of the Minister.
3) Keeping the personal file of a prosecutor in a manner that prejudices the right of the prosecutor stated in sub Article (1) of this Article or detaching a document from the personal file with the intention to either cause damage or benefit the prosecutor is prohibited.
4) Medical reports of a prosecutor furnished in accordance with these Regulations shall be kept in special file.
5) It is prohibited to maintain written information in the personal file of a prosecutor without his knowledge.

## *PART SEVEN*
## *Discipline*
## *Section One*
## *Principle*

74. *Objective and Enforcement of Disciplinary Measures*

1) The basic objective of a disciplinary measure is to correct the prosecutor committing an offense and to educate him to perform his duties efficiently and to dismiss him if the corrective measures fail.
2) A prosecutor who derelicts or fails to perform his duties, or commits any other breach of discipline or ethics shall be liable to the measures under these Regulations without prejudice to any civil or criminal liability.

፫· በዲስፕሊን ጉድለት ወይም በሌላው ጥፋት ምክንያት የሚወሰነው ቅጣት ማናቸውም ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ውሣኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊፈጸም ይችላል ፡፡

፸፭· ስለዲስፕሊን ጥፋቶች

፩· የሚከተሉት ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው ፤

ሀ) ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ ፤

ለ) ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በአማላጅ መሥራት ፤

ሐ) ራስን ወይም ሦስተኛ ወገንን ለመጥቀም በጽሑፍ የሠፈረን መረጃ ሀሰት ብሎ ወደ ሐሰትነት መለወጥ፣

መ) ከሥራ ጋር ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ገንዘብ መበደር ፤

ሠ) አግባብ ያለውን ፍሬ ነገር ወይም መረጃ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ለሚመለከተው ባለማሳወቅ ወይም በመደበቅ ውሣኔውን የሚያዛባ ሁኔታ መፍጠር ፤

ረ) ያለበቂ ምክንያት ሥራን በማዘግየት ባለጉዳይን ማጉላላት ፤

ሰ) አእምሮን በሚያደነዝዝ ወይም ሱስ በሚያስይዝ ሕገ ወጥ ዕፅ መጠቀም ፤

ሸ) ሰክሮ በሥራ ላይ መገኘት ወይም በአደባባይ በመታየት የሙያውን ሥነ ምግባርና የመሥሪያ ቤቱን ክብር ማጉደፍ ፤

ቀ) ያለ በቂ ምክንያት ወይም ያለፈቃድ አዘውትሮ ከሥራ መቅረት ፤

በ) በሥራ ቦታ ለሞራልና ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ፣ ድርጊት መፈጸም ፤ ወይም

ቸ) ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት በመሥሪያ ቤቱ ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ፤

ኀ) ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ከባድ ጥፋቶች፤

ነ) በጽሑፍ ወይም በቃል ከመሥሪያ ቤቱ ወይም ከበላይ ኃላፊው የተሰጠውን ግልፅና ሕጋዊ ትዕዛዝ አለመቀበል ወይም ተግባራዊ አለማድረግ ፡፡

፪· የሚከተሉት ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው ፤

ሀ) በሥራው ላይ ተገቢ ጥረትና ትጋት አለማሳየት ፤

ለ) ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመግባባት ተባብሮ መሥራት ባለመቻል በሥራ ሂደት ላይ እንቅፋት መሆን ፤ ወይም

ሐ) አዘውትሮ መበደር ፤

መ) ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ቀላል ጥፋቶችን መፈጸም ፡፡

ንዑስ ክፍል ሁለት

ስለ ዲስፕሊን ጥፋት፣ ቅጣትና ቅጣትን የመወሰን ሥልጣን

፸፮· በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ስለሚወሰኑ ቅጣቶች

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፭ ሥር የተዘረዘሩትን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋቶችን በመፈጸሙ በዲስፕሊን የተከሰሰ ዐቃቤ ሕግ ጉዳይ በዚህ ደንብ በተወሰነው የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ታይቶ ይወሰናል፡፡

፪· ዐቃቤ ሕጉ በተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንደጥፋቱ ክብደት፣

ሀ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ፤

ለ) ከአንድ ወር የማይበልጥ የደመወዝ ቅጣት፣

ሐ) የአንድ የእርከን ደመወዝ ጭማሪ ክልከላ፣

መ) አንድ ደረጃ ዝቅ የማድረግ ፤ ወይም

ሠ) ከሥራ የማሰናበት ቅጣት ፤

ሊወሰንበት ይችላል ፡፡

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ "ሀ" እና "ለ" የተዘረዘሩት ቅጣቶች ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣቶች ሲሆኑ ከ"ሐ" – "ሠ" የተዘረዘሩት ደግሞ ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣቶች ናቸው፡፡

3) Disciplinary measure may be taken for breaches of discipline or for any other offence irrespective of any court action or proceedings.

75. *Disciplinary Offenses*

1) The following are serious disciplinary offenses:
   (a) Taking or soliciting bribes;
   (b) Doing favour through intermediaries with intent to obtain unlawful benefit for himself or for another;
   (c) Falsification of written documents with intent to obtain benefit for himself or for a third party;
   (d) Borrowing money from a member of the public with whom the prosecutor has a contact in discharge of his official duties;
   (e) Creating a situation which leads to an improper decision through negligently or intentionally failing to inform or concealing relevant information or points;
   (f) Creating inconvenience to the public by delay of service without good cause;
   (g) Consumption of narcotic drugs or other illegal substances of such a nature;
   (h) Found drunk in office or at public place thus harming the reputation of the office and the profession.
   (i) Regular absence from work without good cause or without obtaining leave;
   (j) Initiate quarrel at work place;
   (k) Committing any act against moral and good behavior at work place;
   (l) Damaging office property intentionally or with gross negligence; or
   (m) Any other serious offencse of equal level.
   (n) Rejecting or refusing to execute a clear and lawful order given orally or in writing by the Ministry or the superior.
2) The following are simple disciplinary offenses:
   (a) Not showing effort and diligence at work.
   (b) Obstructing the smooth execution of work by not cooperating with colleagues; or
   (c) persistent borrowing;
   (d) Committing such other related offences of simple nature.

*Section Two*

*Deciplinary Offenses, Penalties and Power to Decide*

76. *Disciplinary Penalties.*

1) A charge brought against a prosecutor for a breach of discipline as provided under Article 75 of these Regulations shall be decided according to the disciplinary procedures laid down in these Regulations.
2) Where a peocecutor is found guilty of disciplinary offense he has been charged with, the following penalties may be imposed according to the gravity of the offense:
   (a) a written warning
   (b) a fine not exceeding one (1) month's salary;
   (c) disallowing of the next increment of pay;
   (d) one grade down-grading; or
   (e) dismissal.
3) Disciplinary penalties enumerated under (a) and (b) in sub-Article (2) of this Article are simple disciplinary penalties while those enumerated under (c) to (e) are serious disciplinary penalties.

፸፯· ቅጣት የመወሰን ሥልጣን

፩· ማናቸውም የዲሲፕሊን ጥፋት በዚህ ደንብ በተወሰነው የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ተጣርቶ መፈፀሙ ከተረጋገጠ ሥልጣን ባለው ጉባዔ ውሣኔ ይሰጥበታል

፪· በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የሚቀርብ ክስ የሚታየው በዋናው ጉባዔ ይሆናል።

፫· በቀላል የዲስፕሊን ጥፋት የሚቀርብ ክስ የሚታየው በንዑስ ጉባዔ ይሆናል።

፬· በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ለዋናው ጉባዔ የቀረበ ክስ ሲጣራ በቀላል የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ ዋናው ጉባዔ ራሱ ቅጣት ሊወስን ወይም ወደ ንዑስ ጉባዔ ሊመልሰው ይችላል።

፭· በቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ለንዑስ ጉባዔ የቀረበ ክስ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ ለዋናው ጉባዔ መተላለፍ አለበት ።

፸፰· በዲሲፕሊን ጥፋት የተከሰሰን ዐቃቤ ሕግ ከሥራ አግዶ ስለማቆየት

፩· በዚህ ደንብ መሠረት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ ሪፖርት የቀረበበት ዐቃቤ ሕግ በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም በምክትል ሚኒስትሩ በሚፃፍ ደብዳቤ ከሥራ ታግዶ እንዲቆይ ይደረጋል። እገዳውም ከ፵፭ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ከሥራ የሚታገደው ዐቃቤ ሕግ የታገደበት ምክንያት በጽሑፍ እንዲገለጽለት ይደረጋል ። ተከሣሹ በአካል ካልተገኘ ወይም አድራሻው ካልታወቀ የእገዳው ደብዳቤ በመሥሪያ ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለ፲ ቀናት ተለጥፎ መቆየት አለበት ።

፫· ዐቃቤ ሕጉ በታገደ በ፭ ቀናት ውስጥ ጉዳዩ ሥልጣን ላለው ዲስፕሊን ጉባዔ መቅረብ አለበት ።

፬· የእገዳው ሁኔታና ዓላማው የግድ ከሚጠይቀው ወይም ከሚያስከትለው ክልከላ በቀር በእገዳው ጊዜ የዐቃቤ ሕጉ ሌሎች መብቶችና ግዴታዎች የተከበሩ ናቸው።

፸፱· የእገዳ ጊዜን ስለማራዘም

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፰(፩) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈጽሟል የተባለውን የዲስፕሊን ጥፋት አጣርቶ ለውሣኔ ለማብቃት ያልተቻለ ሲሆን አግባብ ያለው ጉባዔ ሲጠይቅ ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም ምክትል ሚኒስትሩ የእገዳውን ጊዜ በቂ ይሆናል ተብሎ ለገመተው ተጨማሪ ጊዜ ያህል ብቻ ሊያራዝመው ይችላል። ሆኖም የተራዘመው ጊዜ ከአሥራ አምስት የሥራ (፲፭) ቀናት መብለጥ አይችልም።

፹· በእገዳ ጊዜ ስለደመወዝ መያዝ

፩· አንድ ዐቃቤ ሕግ ከሥራው የታገደ እንደሆነ ከሥራው ታግዶ ለሚቆይበት ጊዜ በሙሉ ደመወዙ መያዝ አለበት። ከሥራ የታገደው ዐቃቤ ሕግ ደመወዙ እንዲያዝ የሚጻፈውን ትዕዛዝ በሚመለከት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፱ የተወሰነው አስፈላጊ ማስተካከያ እየተደረገበት ተፈጻሚ ይሆናል።

፪· የነገሩ ሁኔታ ሲመዛዘን ተገቢ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩን የያዘው ጉባዔ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ምክትል ሚኒስትሩ ወይም ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ከሥራ ለታገደው ዐቃቤ ሕግ የደመወዙ ግማሽ እንዲከፈለው ሊፈቅድ ይችላል።

፫· በተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት የሚሰጠው ውሣኔ ዐቃቤ ሕጉን ከሥራ የማያስወጣው ሆኖ ሲገኝ በዓቃቤ ሕጉ ላይ ከሥራ ማስወጣት ያነሰ ቅጣት ቢወሰንበትም ባይወሰን በትም ከሥራ ታግዶ በቆየበት ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል የተያዘበት ደመወዙ ያለወለድ ይከፈለዋል።

77. Jurisdiction

1) Any breach of discipline shall be decided by a commission having jurisdiction in accordance with the procedure laid down in these Regulations after having been properly investigated.
2) Serious disciplinary offense shall fall under the jurisdiction of the higher commission.
3) Simple disciplinary offense shall fall under the jurisdiction of the lower commission.
4) Where a disciplinary offense considered to be of a serious nature is found to be a simple offense by the higher commission, the higher commission may decide the panalty itself or remand it to the lower commission.
5 Where a disciplinary offense considered to be of a simple nature, is found to be a serious offense by the lower commission, the case shall be referred to the higher commission.

78. *Suspension From Duty of a Prosecutor Accused of Disciplinary Offense.*

1) Where it is reported according to these Regulations that a prosector has committed a serious disciplinary offenses, he shall be suspended by a written order of the Vice-Minister or Deputy Attorney General. The period of suspension shall not exceed 45 days.
2) A prosecutor suspended from duty in accordance with subArticle 1.of this Article shal be informed in writing of the reasons for suspension.
3) The case shall be lodged with the discipline commission having jurisdiction within five (5) days of the suspention of the prosecurtor.
4) The rights and duties of the prosecutor remain unaffectedcby the suspension with the exception of such duties and risistent with consditions and aims of the suspension.

79. *Extending period of Suspension.*

Where it is impossible to examine and decide the case within the time limit indicated under Article 78(1) of these Regulations, the Deputy Attorney General or the Vice Minister may upon the request of the appropriate commission, extend the period of the suspension for a time he may think appropriate. However, the extended period shall not exceed fifteen (15) working days.

80 *Withholding of Salary during Suspension.*

1) When a prosecutor is suspended from duty his full salary shall be withheld for the period of the suspension. An order for withholding the salary of the suspended prosecutor shall be carried out by making the nacessary afjustment where the suspension is extended as prescribed in Article 79 of these Regulations.
2) Where the circumstances of the case justify, the vice Minister or the Deputy Attorney General may allow the payment of half of the salary of the suspended prosecutor upon the request of the commission handling the case.
3) Where the alleged breach of discipline does not entail dismissal, the partially or fully withheld salary shall be paid to the concerned prosecutor without interest, whether or not a lesser penalty has been inposed on him.

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለዲስፕሊን አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት

፹፩· የዲስፕሊን ጥፋት ሲፈጸም ክስ ሥልጣን ላለው የዲስፕሊን ጉባዔ የሚመራው አግባብ ባለው የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ወይም ዐቃቤ ሕጉ በሚሠራበት መምሪያ ኃላፊ አማካይነት ይሆናል።

፹፪· የቀረበውን ክስ ስለማጣራት

፩· ማንኛውም ጉባዔ የቀረበለትን የዲስፕሊን ክስ ለማጣራት በሕግ መሠረት ማስረጃዎችን ያሰባስባል አስፈላጊውንም የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት መጠቀም አለበት ።

፪· ጉባዔው የያዘውን ጉዳይ በተገቢ መንገድ በማጣራት ከተገቢ የውሣኔ ሃሣብ ላይ ለመድረስ እንዲችል በዲስፕሊን የተከሰሰው ዐቃቤ ሕግና መሥሪያ ቤቱ እያንዳንዳቸው ጉዳያቸውን በሚገባ እንዲያስረዱ ማድረግ አለበት ።

፹፫· ስለክስ ጽሑፍ

፩· ክስ የቀረበበት ዐቃቤ ሕግ ለቀረበበት ክስ መልስና መከላከያ ለማቅረብ እንዲችል የቀረበበትን ክስ በዝርዝር የሚገልጽ የክስ ጽሑፍ፡፡ ክሱን ለማረጋገጥ የቀረበበትን ማስረጃና ፣ መልስ የሚሰጥበትን ቀን ፣ ሰዓትና ቦታ ከሚገልጽ መጥሪያ ጋር እንዲደርሰው መደረግ አለበት ።

፪· የተከሳሹ ዐቃቤ ሕግ አድራሻ ባለመታወቁ ወይም በሌላ ምክንያት የክሱን ጽሑፍ ወይም መጥሪያ ለተከሣሽ ለመስጠት ወይም በፖስታ አድራሻው ለመላክ ካልተቻለ ዐቃቤ ሕጉ የዲስፕሊን ክስ የቀረበበት መሆኑንና ክሱ የሚሰማበትን ቀን ፣ ሰዓትና ቦታ የሚገልጽ ማስታወቂያ በመሥሪያ ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ፲፭ ቀን እንዲቆይ መደረግ ይኖርበታል።

፫· ዐቃቤ ሕጉ የክስ ጽሑፍ ደርሶት በመጀመሪያ ቀጠሮ ቀርቦ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ማስታወቂያ ከተለጠፈ ማግስት ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ጉባዔው ዐቃቤ ሕጉ በሌለበት ክሱን መርምሮ ይወስናል።

፬· ዐቃቤ ሕጉ ቀርቦ ለመከራከር ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ጉባዔው ክሱን እንደገና እንዲመረምርለት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል።

፹፬· የጉባዔ ውሣኔ

በዐቃቤ ሕጉ ላይ የቀረበው የዲስፕሊን ክስ ሥልጣን ባለው ጉባዔ ከተጣራ በኋላ ፡

ሀ) ዐቃቤ ሕጉን በጥፋተኛነት የማያስጠይቀው ከሆነ ወይም የተከሰሰበት ጥፋት በማስረጃ ካልተረጋገጠ ክሱ እንዲዘጋ ሊያደርግ ይችላል፡

ለ) የቀረበው ክስ በሙሉ ወይም በከፊል በማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ የጥፋቱን ክብደት በማመዛዘን እንደነገሩ ሁኔታ ከባድ ወይም ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል።

## ንዑስ ክፍል አራት
## ስለይግባኝ

፹፭· የይግባኝ መብት

፩· ዋናው ጉባዔ በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩ በይግባኝ እንዲታይለት ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል። ሚኒስትሩ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## *Section Three*
## *Disciplinary procedure*

81 *Lodging of charges*

Where a disciplinary offense is committed, the charge shall be directed to the disciplinary co;;ission having jurisdiction by the head of the appropriate branch office of the Ministry or by head of the department where the prosecutor is working.

82. *Investigation of the charge*

1) For purposes of investigating disciplinary charges, every commission shall, in accordance with law, establish facts, collect evidences and apply the necessary procedure.

2) In order for the commission to arrive at appropriate decision propsal, it shall give proper hearing to both the prosecutor charge and the Ministry who brought the charge.

83. *Charge Sheet*

1) Where a prosecutor is charged with a disciplinary offense, he shall be provided with a charge sheet containing all facts which constitute the breach of discipline, the evidence brought to prove the case together with summons which indicates the date, time and place where he presents his defense.

2) Where it is not possible to deliver the charge sheet or summons to the proseutor or his whereabout is not known to send same by postal service, the summons indicating the charge brought against the prosecutors the date, time and place of the hearing shall be affixed on the notice board of the Ministry for fifteen (15) days.

3) Where the prosecutor fails to appear at the hearing after receiving the charge or fails to appear within thirty (30) days of notification on the notice board as provided in sub-Article 2 of this Article, the commission shall hear and decide the case in his absence.

4) Where the prosecutor shows that his failure to appear before the commission was due to force majeur, he has the right to request the commission for re-examination of the case.

84. *Decision of the Commission*

The commission having jurisdiction over the charge brought against the prosecutor, after proper examination, shall:

(a) dismiss the charge where the charge could not be established or there was no sufficient evidence to justify conviction.

(b) Impose a serious or simple disciplinary penalty taking in to consideration the gravity of the offense committed by the prosecutor concerned.

## *Section Four*
## *Appeal and Re-examination*

85. *Right to Appeal*

1) An appeal may be filed against the decision of the higher Commission to the minister. The decision of the minister shall be final.

፪· የይግባኝ አቤቱታ ውሣኔው ለዐቃቤ ሕጉ ከደረሰበት ቀን ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ በሰላሣ (፴) ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት መቅረብ አለበት። በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበ የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም።

፹፮· <u>ስለይግባኝ ማመልከቻ</u>

በይግባኝ ማመልከቻው ላይ ይግባኝ ባይ ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ የሚቃወምበትን ምክንያት በዝርዝር በየአርዕስቱ በመለየትና እንዲቀየርለት ወይም እንዲሻሻልለት የሚፈልገውን ጉዳይ በግልፅ ማመልከት አለበት።

፹፯· <u>ስለወጭዎች</u>

የዲስፕሊን ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ ምሥክር፣ ኤክስፐርት ወይም ሌላ ማስረጃ በማቅረብ ረገድ የሚደርሰውን ወጭ ማስረጃ እንዲታይለት ወይም እንዲሰማለት የሚጠይቀው ወገን መክፈል አለበት። ሆኖም ዐቃቤ ሕጉ በቀረበበት የዲስፕሊን ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ ለክርክሩ ያወጣው ወጭ በሚኒስቴሩ ይተካለታል።

<u>ክፍል ስምንት</u>

<u>ስለዋና ጉባዔና ንዑስ ጉባዔዎች</u>

፹፰· <u>መቋቋም</u>

፩· የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ዋና ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ) በሚኒስቴሩ ዋና መሥሪያ ቤት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪· በሚኒስቴር ዋና መሥሪያ ቤትና የሚኒስቴሩ ተጠሪ ጽ/ቤቶች በሚገኙባቸው ክልሎች የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ንዑስ ጉባዔዎች ተቋቁመዋል።

፹፱· <u>የዋናው ጉባዔ አባላት</u>

፩· ዋናው ጉባዔ በሚኒስትሩ የሚሰየሙ የሚከተሉት አምስት አባላት ይኖሩታል፣

ሀ) አንድ ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ....... ሰብሳቢ
ለ) አንድ ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ... ም/ሰብሳቢ
ሐ) ሁለት ም/ረ/ጠ/ዐቃብያነ ሕግ .......... አባላት
መ) አንድ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ ..... አባልና ፀሐፊ።

፪· የዋናው ጉባዔ ሰብሳቢ ምክትል ሰብሳቢና አባላት ሆነው የሚሰየሙት ዐቃብያነ ሕግ በሥራ ልምዳቸው፣ በሕግ ዕውቀታቸው፣ በከፍተኛ የሥራ አፈጻጸም ውጤታቸው፣ በታታሪነታቸው፣ በታማኝነታቸው በፍትሐዊነታቸውና በሥነ ምግባራቸው መልካም ስም ያተረፉና በሥራ ባልደረቦቻቸው ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ የሚታመንባቸው መሆን አለባቸው።

፺· <u>የዋናው ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

ዋናው ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩· ደረጃቸው ከምክትል ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በታች የሆኑ ዐቃብያነ ሕግን ቅጥር፣ ሹመትንና ዝውውር በሚመለከት ለሚኒስትሩ የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል።

፪· የሥራ ኃላፊነት ደረጃቸውን እንደገና የመመደብን፣ድርጅታዊ መዋቅርን፣ የደመወዝ ስኬልና የውሎ አበል አከፋፈልን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማድረግ ወይም በማስጠናት ለሚኒስትሩ የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል።

፫· ይህን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ልዩ ልዩ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችን ፣ የአሠራር ሥነ ሥርዓቶችን ፣ መመዘኛዎችንና ቅጾችን እያዘጋጀ ለሚኒስትሩ ያቀርባል ፣ ሲፀድቅም አፈጻጸማቸውን ይከታተላል።

፬· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፱ መሠረት በአንድ ዐቃቤ ሕግ ላይ በሚደርስ የችሎታ ማነስ ዘገባ ላይ ስለሚወሰደው እርምጃ የውሣኔ ሃሣብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል።

2) An appeal shall be filed by the prosecutor to the office of the Minister within thirty (30) days of the receipt of the decision or its notification on the notice board. An appeal filed out of time may not be accepted.

86. *Memorandum of Appeal*

The memorandum of appeal shall show in detail and under distinct headings the grounds of objection to the decision appealed against and shall state clearly the nature of the relief sought.

87. *Expenses*

The expenses concerning witnesses, expert or other evidences brought before the disciplinary hearing shall be borne by the party who brought them. However, the expenses shall be be reimbursed to the prosecutor by the ministy where he is found not-guilty of the disciplinary charge.

<u>*PART EIGHT*</u>

<u>*The Higher Commission and Lower Commission*</u>

88. <u>*Estabishment*</u>

1) Prosecutors' Administration Higher Commission, herein after referred to as "the Higher Commission" is hereby established by these Regulations within the head office of the Ministry.
2) Prosecutors' Administrtion Lower Commissions are hereby established in the Head office and branch offices of the Ministry in national regional states.

89. <u>*Members of the Commission*</u>

1) The Higher Commission shall have the following five members appointed by the minister:
   (a) One Assistant Attorney General.... Chair person
   (b) One Assistant Attorney General.... Vice Chairperson
   (c) Two Deputy Assistant Attorneys General... members
   (d) One senior Prosecutor........ member and secretary.
2) Prosecutors appointed as chair person, vice-char person and members of the Higher Commission shall have good reputation for their legal knowledge and experience, for their efficiency, diligence, integrity, sense of justice, good conduct and for having won the confidence of their colleagues.

90. <u>*Powers and Responsibility of the Higher Commission*</u>

The Higher commission shall have the following powers and responsibilities:

1) to recommend to the minister the employment, transfer and appointment of prosecutors below the rank of Deputy Assistant Attorneys General.
2) to study or cause to be studied and make recommendations to the minister on matters concerning the organizational structure, re-classification of position, salary scale and payment of allowances and per diem.
3) to prepare and submit to the minister and follow up their implementtion upon approval of guidelines, procedures, criteria and formates as may be necessary for the implementation of these Regulations.
4) to make recommendations to the minister of the measures to be taken on inefficiency reports of a prosecutor submitted in accordance with Article 59 of these Regulations.

፭· በዚህ ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዲስፕሊን ጉዳዮችን መርምሮ ይወስናል።
፮· በዚህ ደንብ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፺፩· የንዑስ ጉባዔ አባላት

፩· ንዑስ ጉባዔው፣ በሚኒስትሩ የሚሰየሙ አንድ ሰብሳቢና ሁለት አባላት ይኖሩታል።
፪· የተጠሪ ጽ/ቤት ኃላፊ የንዑስ ጉባዔው አባል ሆኖ አይሰየምም ።
፫· ንዑስ ጉባዔው ድምፅ የመስጠት መብት የሌለው አንድ ዐቃቤ ሕግ በፀሐፊነት ይመድባል።

፺፪· የንዑስ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

፩· ንዑስ ጉባዔው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዲስፕሊን ጉዳዮችን መርምሮ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል ።
፪· በክልሉ ተመድበው እንዲሠሩ በክልሉ ስለሚመለመሉ ዐቃቢያነ ሕግ አመራረጥ፣ ቅጥርና ሹመት አስተያየቱን ለዋናው ጉባዔ ያቀርባል።
፫· በተጠሪ ጽ/ቤት ሥር ተመድበው የሚሠሩ ዐቃብያነ ሕግ በያዙት የሥራ መደብ በክልሉ ውስጥ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር የሚያቀርቡትን ጥያቄ እየመረመረ አስተያየቱን ለዋናው ጉባኤ ያቀርባል።
፬· በዚህ ደንብና በዋናው ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፺፫· የጉባዔዎች የአሠራር ሥነ ሥርዓት

የእያንዳንዱ ጉባዔ የአሠራር ሥነ ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፣

፩· በማናቸውም ስብሰባ ከአባሎቹ ፪/፫ኛ ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይኖራል።
፪· ማናቸውም ጉዳይ በስብሰባው በተገኙ አባሎች በድምፅ ብልጫ ይወሰናል።
፫· የጉባዔው አባላት ድምጽ እኩል ከሆነ የጉባዔው ሰብሳቢ ያለበት ወገን ውሣኔ የጉባዔው ውሣኔ ይሆናል።
፬· ጉባዔው በድምፅ ብልጫ በሚወሰንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው ድምፅ አስተያየት ከነምክንያቱ በስብሰባው ቃለ ጉባዔ መመዝገብ አለበት።
፭· አስፈላጊ ሲሆን ጉባዔው የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የራሱን የሥራ አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል።

ክፍል ዘጠኝ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

ዝርዝር መመሪያዎች ስለማውጣት

፺፬· ሚኒስትሩ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

፺፭· ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም·

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

5) to decide disciplinary cases in accordance with the powers conferred on it under these Regulations.
6) to carry out other responsibilities entrusted to it by these Regulations.

91. *Members of the Lower Commission*

1) The Lower commission shall have one chair-person and two members apointed by the minister.
2) The head of the branch office may not be appointed as member of the lower Commission.
3) The lower commission shall appoint a prosecutor as a secretry with no-voiting rights.

92. Powers and Responsibility of the Lower Commission

The Lower commission shall have the following powers and responsibilities:

1) to give a final decision on disciplinary cases as indicated under Article 77(3) of these Regulations.
2) to make recommendations to the Higher commission on the selection, employment and appointment of prosecutors working for and recruited from Regions.
3) to make recommendation to the Higher commission on transfer requests of prosecutors working in branch offices within the branch office locality.
4) to carry out other responsibilities entrusted to it by the Higher commission and these Regulations.

93. *Rules of Procedures of Commissions*

The rules of procedures of each commission shall be as follows:

1) There shall be a quorum where two-thirds (2/3) of the members are present at the meetings of the commission.
2) All matters shall be decided by a majority vote of the members present.
3) In case of a tie, the chair-person shall have a casting vote.
4) Where decisions are taken by a majority vote the dissenting opinion of the minority shall be recorded.
5) Where necessary the commissions may, without prejudice to the provisions of this Article, draw up their own rules of procedure.

*PART NINE*

*Miscellaneous Provisions*

94. *Power to issue Directives*

The Ministry may issue directives for the implementtion of these Regulations.

95. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the day of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 20th day of November 1998.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA